የካህኑና የጠንቋዩ ወግ



ካህኑና ቁሱ በሚስጥር ተወዳጅተው የሚኖሩ የልብ ጓደኛሞች ናቸው፡፡ ጓደኝነታቸው በጥቅምም የተሳሰረ ነው፡፡ ጠንቋዩ አብዛኛው ተማሪ የማያውቀውን ጉዳይ እያነፈነፈ ያገኛል፡፡ ለካህኑም ይመግባል፡፡ ካህኑ ደግሞ ምግብና መጠጥ እንደ እጅ መንሻ አድርጎ እነዚህን ትኩስ መረጃዎችን ይቃርማል፡፡ ዛሬ ደግሞ በተማሪዎች ሕብረት አካባቢ ስለተነሳው ማዕበል (የፐሬዚደንቱን መነሳት ሽክሽክታ) ተያይዞ ስለሚወራው የሙስና ጉዳይ(እውነት ከሆነ)፣ ዋናው የተማሪዎች ሕብረት (የአሪዱ) እጁን ማስገባት እና ሌሎች ትኩስ መረጃዎች ለመቃረም ካህኑ በመረጃ ርሃብ እየተቃጠለ ከዚህ ረሃቡ ይገላግለው ዘንድ ከመረጃ እንጀራው ወደ ሚያጎርሰው ጠንቋይ ጓደኛው ጠርሙስ ሙሉ ባለዛፍ አረቄ ይዞ ከቤቱ ደጃፍ ቆሟል፡፡

ጠንቋዩ፡- ስንት ጊዜ ነገርኩህ? ይህ ቤት እኮ ያንተም ቤት ነው፡፡ ግዴለም ገብተህ አረፍ በል፡፡

ካህኑ፡- አይ! የቤቱን ነገር እንኳ ተወው፡፡ ይልቅ ይህችን ነገር ያዝ ለሰሞኑን ብርድ ትሆንሃለች፡፡... ብሎ አንገቱ በእጅ ላብ የራሰውንና በጋዜጣ የተጠቀለለ ጠርሙስ እያቀበለው ዐይኖቹን መቀመሚ ፍለጋ አንከራተታቸው...

ጠንቋዩ፡- (ባንድ እጁ እንደ አብራኩ ክፋይ የሚወድደውን አረቄ እየተቀበለ በሌላኛው እጁ ቡትቶ ወደተከመረበት ያረጀ ዱካ እያመራ) "ሀ! ሀ! ዛሬ ጮማ ጉዳይ ፈልገህ መሆን አለበት የመጣኸው?..." መልሱን ሳይጠብቅ እንዲያውም "ስለሰሞኑን የተማሪዎች ህብረት አወዛጋቢ ጉዳይ ልትጠይቀኝ ነው የመጣኸው?" ፍፁም መረጋጋት ውስጥ ሆኖ ቀጠለ፡፡

ካሕኑ፡ አፉን በጋቢ ሸፍኖ ሰርቆ እንደተያዘ ሌባ ቁልቁዮ ቁልቁዮ ሲል ከጠንቋዩ የሚወጡት ቃላት እንደዥረት እየፈሰሱ በእርጋታ ከካህኑ ጆሮ ይዘልቃሉ፡፡

ጠንቋዩ፡- "አዎን እውነት ነው! ቁመተ ለጋው ገራገር ፊት ያለውና ሁሌም ጊቢ ውስጥ እንደሸማኔ መወርወሪያ አለረፍት ወዲያ ወዲህ የሚለው ያለፈው አንደኛ መንፈቅ አመት ፕሬዚደንት የሆነው ግዛቸው በፕሬዚዳንትነት መቀጠሉ አክተሟል፡፡ የቀድሞ ምክትል ፕሬዚዳንት መልከመልካሙና ፀባየ ቀናው አድናን እርሱን ተክቶ ይሰራል ነው የሚባለው፡፡" ዘለግ ያለ ፀጥታ የበሬ ግንባር የማታክለውን የጠንቋዩን ቤት አፈነው፡፡ ዝምምምምምምምታ

ካህኑ፡ "ምክንያቱ ምንድነው?" ብሎ በጎርናና ድምፅ ቤቱን ያፈነውን ቀፋፊ ፀጥታ ድባብ ባጭር ቃል ገፈፈው፡፡ የሁሉን አዋቂነት በምትመስለው አጭር ፈገግታ ገረፍ አድርጎት ያረቁውን ጠርሙስ ካጭር ትግል በኋላ ከፍቶ ከካህኑ ትከሻ ትይዩ ለደንቡ ያህል ቁም ሳጥን መስሎ ከቆመው የእንጨት መደርደሪያ ብርጭቆ እንዲያቀብለው በምልክት ጠቆመው፡፡ ካህኑ ፈጠን ብሎ የታዘዘውን ፈፀመ፡፡

ጠንቋዩ፡- ብርጭቆውን እየሞላ "ወዳጄ! ነገሩ ብዙ ነው፡፡ ለኔ ለጠንቋዩ እንኳን በደንብ አልተገለጠልኝም፡፡ ግን በግልፅ ከሚነገሩት ምክንያቶች መካከል..." ወሬውን በድንገት በእንጥልጥል አቁሞ በግራ እጁ የያዘውን አነስተኛ ብርጭቆ ሙሉ አረቄ ጨለጠው፡፡ "እ...ኽ! ኽ! ኽ!".... የጨለጠው አረቄ ከላንቃው ጀምሮ የጎሮሮውን አራቱን ማዕዘን እየቀደደ ሲወርድ ካሰማው የሰቆቃ ድምፅ ባሻገር ፊቱ ላይ ሲቃው በግልፅ ይታያል፡፡ በተቃራኒ አቅጣጫ የተንጠለጠሉት ሁለት ጉንጮቹ፣ ሰፊው ግንባሩና ሾል ያለው አገጩ ባንድነት ጭምድድ ብለው መሐል አፍንጫው ስር ተሰበሰቡ፡፡ ወዲያው ደግሞ ተመልሰው ከቦታው ላይ በመቀመጣቸው ሁለተኛውን እየቀዳ "አቅም የለውም! የመሪነት ቅርፅ በጭራሽ አልፈጠረበትም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ስልጣኑን ያላግባብ ተጠቅሞ ከስምንት ሺህ ብር በላይ ለግል ጥቅሙ አውሏል! ይህ ሳይንስ በወዳጅነት ተነሳስቶ ለGC ኮሚቴ ማህተም እንዲሰሩ ፈቅዷል፡፡ እንደሚታወቀው ከተማሪ ህብረቱ ውጭ ያለ ማንኛውም በተማሪ ሚመራ ክበብ ጊዜያዊም ሆነ ቋሚ ማህተም እንዲኖረው አይፈቀድም፡፡ የጊቢው ሕግ ነው፡፡ ታዲያ ይህን ሕግ ተላልፎ የGC የኮሚቴው ራሱ ማህተም አሰርቶ ከገንዘብ ጋር የተነካካ ጨዋታ ውስጥ ዘው ብሏል ይላሉ ከሳሾቹ..." ብሎ አሁንም ሁለተኛውን ብርጭቆ ጨለጠው፡፡

ከመጀመሪያው ባነሰ መልኩ ገፅታው መጠነኛ ለውጥ ከማሳየት ውጭ አላጓራም፡፡ ካህኑ በደመነፍስ ከመቀመጫው ወደፊት ሰገግ ብሎ የጠንቋዩ አፍንጫ ስር ሊገባ የስንዝር ታክል ርቀት ቀርቶታል፡፡ "ደሞኮ ገንዘቡን መጠቀሙን አምኗል አሉ" አሁን ካህኑ ከወንበሩ ወደኋላ መለስ ብሎ የቀድሞ ቦታውን ያዘ፡፡

ድህረ-ታሪክ

ካህኑ የሰማውን እያሰላሰለ ወደቤቱ ጉዞ ጀምሯል፡፡ ለካስ ሳያውቀው በጠንቋዩ ቤት ሰዓቱ ተተኩሶ ኖሯል...

"ዋናው የተማሪ ህብረት በዚህ ጊቢ የተማሪ ህብረት ውስጥ እጁን ማስገባት የሚችለው ምን ያህል ነው?" በራሱ በማይመለስ ዋያቄ እየተጨነቀ... መልሱን እየገመተ...አንዳንዴም በገረም ለብቻው ፈገግ እያለ ጉዞውን አጋመሰው፡፡ "ከሳሾቹ ማን ናቸው? የተከሳሹን ጉዳይ የሚያይ ከሁለቱም ወገን ያልሆነው (Neutral body) ተቋቁሟል ወይ? ሕብረቱ ራሱ አንድን በተማሪ ፓርላማ የተመረጠ ፕሬዚደንት ማውረድ ይችላል? ያውም ለፓርላማው ጉዳዩ ሳይቀርብ ይህን ሁሉ ነገር የሚፈታው በእርግጥ የሕብረቱ ህገ-ደንብ ነው? ታዲያ የህብረቱ ሕገ-ደንብ ምን ይላል?" የሚለውን ለመመለስ ህጉን ማየት እንዳለበት አምኖ ሕጉን ፍለጋ ጀመረ...

ማንን እናመሰግን?

ተማሪው ከትምህርቱ ጎን ለጎን በጊቢ ውስጥ ተሳትፎ እንዲደርግ በመጀመሪያ የራሱ የተማሪው መነሳሳት ቅድሚያ የሚጠበቅ ቢሆንም ምቹ ሁኔታ እና "አይዟችሁ ከጎናችሁ ነን" ባይ ከሌለ የተማሪው መነሳሳት በራሱ አንድ እርምጃ ተራምዶ ለውጤት እንደማያበቃ ለማወቅ የተለየ ጥናት አያስፈልግም፡፡

ለMULSSA VOICE (የሕግ ተማሪዎች ድምፅ) እንደገና ህይወት መዝራት አዲሱ የመልሳ ፕሬዚደንት ከኤዲቶሪያል መነቃቃትና የሕግ ትምህርት ቤት ዲን አቶ ምህረተአብ ገ/መስቀል ግደብ የሌለው ያላሰለሰ ጥረት "አይዟችሁ" ባይነት ከዚያም አልፎ ላጠቃላይ የሕትመት ሥራው የቢሮ ፕሪንተራቸውን ለዚሁ ተግባር መተባበራቸው በእውነቱ ለተማሪው ከትምህርት ገበታው ከሚያገኘው የዘወትር እውቀት ባሻገር እንደዚህ ካሉ አጋጣሚዎች ለሚያገኘውና ለሚያዳበረው ክህሎት አጠቃላይ የመፅሄቱ ኤዲቶሪያል ክፍል እና መልሳ ከልብ የመነጨ ምስጋና እያቀረበ የዚህ አይነቱ ፍፁም ቅን ልቦናን የተሞላ ያስተዳደር ባህል እንዲጎለብት ይመኛል፡፡በተጨማሪም መረጃዎችን በመስጠት፣ ልምድ በማካፈል፣ በማበረታታት ይህ መፅሄት እውን እንዲሆን የበኩላችሁን አስተዋፅዖ ያደረጋችሁትን ለስማችሁ ቦታ ቢያንሰንም ለስራችሁ ግን ምስጋናችን ልባዊ ነው፡፡ /ኤዲቶሪያል/

ዘመቻ ቫንዳል Students

በዘላለም አ. (zola48@yahoo.com)

ሠላም ለናንተ ይሁን ውድ ወገኖቼ እንዴት አላችሁ? መቼስ ያው ለወጉ ያህል ሰላምታ ልስጥ ብዬ ነው እንጂ ሰላም እና ተሜ ብዙ ጊዜ አብረው አይቆዩም፡፡ ፈተናው፣ መኖው (በተለይ ለነን ካፌ)፣ የ"ቺኮች ጉተታ"፣ የሌክቸር "ሀርደኛ" ተሜው እና ሰላሙ መሃል እየገባ መበጥበጡ ግልፅ ነው፡፡ ግና ተሜ መሆን አለም ነው! ደስታ ነው! ለምን አትበሉኝ? አስቡት እስኪ የእውቀት መቃረሙ፣ "ላይሰንስ" ያለው ፈላጭ መሆኑ፣ ለስልጣኔና ለቴክኖሎጂ ቅርብ መሆኑ... አረ ምኑ ቅጡ... ብቻ በደፈናው የተሜ ኑሮ ከሌላው ማህበረሰብ የተሻለ ነው ማለት ያቻላል፡፡ ለዚህም ይመስለኛል እድሜዬ ለትምህርት ከደረሰ ጀምሮ ዩኒቨርሲቲ መግባት አእምሮዬ ውስጥ ሰርፆ የቀረ ሕልሜ የሆነው፡፡ ግን ምን ያደርጋል "ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ" እንደሚሉት አበው፣ የኔ ሕልምና ይህ ጊቢ በተለያዩ ምክንያቶች ፊፅሞ እየተራራቁ ሦስት አመት ተጠጋ፡፡ ሦስት ዓመታት ሙሉ ሲያስቆጩኝ ሲያበሳጩኝ የነበሩ፣ የኔን ሕልምና ይህን ጊቢ ሲያራርቁ የነበሩ ጉዶች ወይ "እዛ" ነበሩ ተብለው ሊቀረፉ አልያም ያንተ ሕልም "የቀን ቅዠቶች ናቸው ወደ ቀልብህ ተመለስ" ሊሉኝ 2009ን አስታክው ከተፍ አሉ፡፡



ነገሩ እንዲህ ነበር የሆነው...

የሕግ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ማህበር (መልሳ) ዓመታዊ የአመራሮች ምርጫ ተካሄደ፡፡ በዚህም ምርጫ እስከዛሬ በስም ብቻ የተቀመጠውን፣ በስራ ግን ያለ የማይመስለውን MULSSA'ን ትጉህና ሰርቶ የሚሰራ አመራር አገኘ፡፡ ይህም ልጅ ይህን የተኛ ማህበር እንደገና ቀስቅሶ የሕግ ተማሪዎች ድምፅ በተሰኘ መፅሄት እስቲ እንወቃቀስና ሌሎች ርዕሶችን አካትቶ እኔንና እናንተን አገናኘን፡፡ አዎን መወቃቀስ ተገቢ ነው፡፡ ይሞርዳል፣ ያስተካክላል፣ የተሻለ ደረጃን ያስይዛል፣ ተገቢ ያልሆኑ አስተሳሰብና ልማዶችን ያስቀራል፡፡ ለዚያም ነው ከላይ እንደጠቀስኩት ለእኔም ለእናንተም መፍትሔ ይሰጣል ያልኩት፡፡ በዚህ ከተስማማን ዛሬ የምንወቅሰው የቫንዳሊዝም ወረርሽኝ ያጠቃቸውን ተሜዎችን ነው፡፡

ቫንዳሊዝም (Vandalism) ማለት አንድን የጋራ ወይም የግል የሆነን ንብረት ያለምንም ጥቅም በፍቃደኝነት ማጥፋት/ማበላሸት ማለት ሲሆን ይህ ቃል የመጣውም ከጥንት የጀርመን ሕዝቦች የነገድ ስያሜ ነው፡፡ ቃሉ ከማጥፋትና ከማበላሸት ጋር እንዲቆራኝ ያደረገው በ455 ዓ.ም አካባቢ እነዚህ ሕዝቦች ከምእራብ ሮማን መንግስት ጋር ባደረጉት ጦርነት ቫንዳልሶች አሸንፈው "ከተማዋን" ሲወሩ "ከተማዋ" ውስጥ የነበሩ ንብረቶችን አውድመው ነበር፡፡ የቫንዳልሶች አውዳሚነት በወቅቱ ከነበሩ ሌሎች ወራሪዎች ጋር ሲነፃፀር እጅጉን የላቀ ነበር፡፡ ታዲያ ይህ ከእኛ ጋር ምን አገናኘው ብሎ የሚጠይቅ አንባቢ አይጠፋም፣ ተገቢ ጥያቄ ነው፡፡ እኔም ይህን ፅሁፍ የፃፍኩት ስለ "ጀርመን" ሕዝቦች አጥፊነት ለማሳወቅ ፈልጌ አይደለም፡፡ ይልቅ ከላይ እንደገለፅኩት ከሕልሜ አጨናጋፊ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል አንዱና ዋነኛው የሆነው የቫንዳሊዝም ወረርሽኝ አለቃ መርጦ ቅርፅ እቀያየረ በከባዱ እየተስፋፋ መሆኑን ባለፈው ካፌና እንዳንድ ቦታዎች ላይ ማስታወቂያ ተለጥፎ በማየቴ በጣም አስደንግጦኝ ነው፡፡ ማስታወቂያው ባጭሩ እንዲህ ይላል፡፡

"በትናንትናው ዕላት በዋናው ቤተ-መፅሐፍት አካባቢ ማንነቱ ያልታወቀ ተሜ ጨለማን ተገን አድርጎ ተረፈ ምርቱን በኮዳና በካርቶን አስቀምጦ ሔደ" ይላል፡፡ (በነገራችን ላይ ሴት ልትሆንም ትችላለች)



በጣም ያሳፍራል፡፡ የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ ይህንን ድርጊት የፈፀመው አለቃው ቫንዳሉ ተሜ ሆኖ ግብረ አበሮቹ በየዶርሙ ተሰግስገው ይገኛሉ፡፡ ለአለቃቸውም ሽልማት ሁሉ ሰጥተዋል አሉ፡፡ ጉድ እኮ ነው!

እንዳለመታደል ሆኖ እዚህ ጊቢ ውስጥ ብዙ ነገሮች የጋራ መጠቀሚያና መገልገያዎች ናቸው፡፡ ሽንት ቤት፣ ባኞ ቤት፣ የልብስ ማጠቢያ ገንዳ፣ ዶርም ወዘተ...በጋራ ነው የምንጠቀመው፡፡ እዚህ ጊቢ እስካለን ድረስ እነዚህ ንብረቶች የኛ የሁላችን የጋራ ንብረቶች ናቸው ማለት ነው፡፡ የሥነ-ምህዳር (Ecology) ምሁር ሆነው ጋሬት ሃርዲን በ Tragedy of the commons *ፅሁፉ* ላይ እንዳተተው *...አንድን ነገር በጋራ ስንጠቀም የኔነት ስሜት ስለማፈጥርብን በማይገባ አኳኋን ይበዘበዛል... ለዚህም መፍትሔው ነገሮችን በግለሰብ ደረጃ መጠቀም ነው...* ይለናል፡፡ ሃርዲን ፅሁፉን የጻፈው የጋራ ንብረት በሆነው መሬትን በሚመለከት ቢሆንም አንድ ስሙን የማላስታውሰው በሐርዲን ፅሁፍ ላይ አስተያየቱን የሰጠ ምሁር... ይህ ፅሁፍ በጋራ መጠቀሚያ ለሆኑ ነገሮች ሁሉ እንደሚሰራ አትቷል፡፡ የሐርዲን ሓሳብ በብዙ ምሁራን ዘንድ ትክክል እንደሆነ ቢታመንበትም በኢኮኖሚ ደካማ በሆኑ ሀገራት ላይ ተቀባይነት ማግኘቱ አዳጋች ነው፡፡

በ455 ዓ.ም አካባቢ እነዚህ ሕዝቦች ከምእራብ ሮማን መንግስት ጋር ባደረጉት ጦርነት ቫናዳልሶች አሸንፈው "ከተማዋን" ሲወሩ "ከተማዋ" ውስጥ የነበሩ ንብረቶችን አውድመው ነበር፡፡ የቫንዳልሶች አውዳሚነት በወቅቱ ከነበሩ ሌሎች ወራሪዎች ጋር ሲነፃፀር እጅጉን የላቀ ነበር፡፡

የስፖንሰር ቦታ

0920 66 65 95

በተለይ እንደኛ ያለ ሀገር ላይ የጋራ መጠቀሚያዎችን በግል ለማዳረስ አቅማችን አይፈቅድም፡፡ ይህን ስል ታዲያ እነዚህ ነገሮች ያላግባብ ይበዝበዙ ወይም ይበላሹ ማለቴ አይደለም፡፡ ይልቁንም የሰው ልጅ በታሪኩ ከቀደመው ጊዜ ጀምሮ ለችግሮቹ መፍትሔ እያበጀ እዚህ ደርሷል፡፡ እኛም በጋራ የምንጠቀማቸው ንብረቶች በተቻለን አቅም እንዳይበዘበዙ/እንዳይበላሹ መፍትሔ ማበጀት እንችላለን፡፡ ከእነዚህ የጋራ መጠቀሚያ በዝባዦች አንደኛውንና ዋነኛውን የሆነውን ቫንዳሊዝም የተባለ ወረርሽኝ ከግቢያችን ነቅለን እናስወጣለን !!፡፡ ባብዛኛው ጊዜ ብዙዎቻችን እንደምንታዘበው በኒቢያችን ያሉ የጋራ መጠቀሚያ ንብረቶች የተበላሹና የተጎዱ ናቸው፡፡ ይህም የመማር ማስተማሩን ሂደት ባያሌው ተፅዕኖ ያመጣል፡፡ ለዚህም ማሳያ ዶርሞቻችንን፣ ሽንት ቤቶቻችንን፣ ማየቱ በቂ ይመስለኛል፡፡ አባዛኛዎቹ ሽንት ቤቶችና ዶርሞቻችንን ካላግባብ አጠቃቀም በሚመጣ ለጤና ጠንቅ የሆነ ሽታ፣ ግድግዳዎቹ ቀለማቸው የተፋፋቀ፣ ሎከሮች መዝጊያዎቻቸው የተሰባበሩ፣ የጓሮ በሮችና መስኮቶች መስተዋት የተሰባበሩ ናቸው፡፡ ይህን ያደረገው ሌላ ማንም ሳይሆኑ እነዚሁ ቫንዳል ተሚዎች ናቸው፡፡ ይህም ራሳችንን መልሶ መጉዳቱ ከ"ግልፅ" በላይ ነው፡፡

በመጥፎ ሽታ ምክንያት መታመም፣ ዶርም ውስጥ ያሉ ወንበሮችና ጠረጴዛዎች በመሰበራቸው ምክንያት ዶርም ውስጥ ተመቻችቶ ማጥናት አለመቻል፣ በጓሮ በርና በተሰበሩ መስኮቶች የሚገባው ነፋስ እንቅልፍ ማጣት ወዘተ... ናቸው፡፡ እነዚህ ምክንያቶች የመማር ማስተማሩን ሂደት ላይ የሚያመጡት አሉታዊ ተፅዕኖ የከፋ ነው፡፡ በማደሪያ ሕንፃዎች ያሉ የሻወር ቤት ቧንቧዎች በመሰበራቸው ምክንያት የሚባክነው ውሀ ሳያንስ ከዚህም በተጨማሪ ብዙ ተማሪዎች በሕንፃ-13 ጀርባ የልብስ ማጠቢያ ቦታ ላይ ለመታጠብ ተገድደዋል፡፡ ወንድስ ሜዳ ላይ መታጠቡ ብዙም አይከብደውም ይሆናል ግን አስቡት እስቲ ይህ ጉዳይ ለሴት እህቶቻችን ምን ያህል ፈተና እንደሚሆን፡፡ የሽንት ቤቶች ሽታ አላስቆም አላስቀምጥ ይላል፡፡ እነዚህን ቫንዳል ተሚዎች ሽንት ቤቱን ሲጠቀሙ *"መሃሉን በሳተ"* አስመስለውታል፡፡ ከዚህ የሚብሰው ደግሞ ዳር "መጠቀማቸው" ሳይንስ በርሜል ውስጥ ውሃ እያለ ሳይደፋበት *"እንደ ጥሩ እቃ"* ጥለውት መውጣታቸው ነው፡፡ የበለጠ የሚያስገርም የሚሆነው ደግሞ አንድ የእነርሱዉ አባል ይመጣና እርሱም እንደገና ውሀ ሳደፋበት አጠገቡ አስቀምጦ ይሄዳል፡፡

እኔኮ ወገኖቼ ድንቅ የሚለኝ፣ እነዚህ ሰዎች አስራ ሶስት ዓመት ጫካ ነው እንዴ ያሳለፉት፡፡ ይህ ነገር እኮ መጥፎ ሽታ እንደሚያመጣ የአምስት ዓመት ልጅ እንኳን ያውቃል፡፡ እንደ'ኔ ይህ ዓይን ያፈጠጠ መሀይምነት ነው፡፡ እንዲውም ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ከጨለማው ዘመን አስተሳሰብ ያልተላቀቀ ሰው ነው ብሎ ለመናገር ያስደፍራል፡፡ እጁን የታጠበበትን ቧንቧ ከፍት ጥሎ መሄድ፣ የጋራ መማሪያ ክፍሎች ግድግዳ ላይ ይባስ ብሎ አስፀያፊ ነገር መፃፍ፣ የመማሪያ መፃሕፍት ላይ መፃፍና መቅደድ እና የመሳሰሉት ከአንድ ምክንያታዊ ሰው የማይጠበቁ ድርጊቶች ናቸው፡፡ ይህን የሚያደርግን ተሚም ቫንዳሊዝም የተባለ ወረርሽኝ ይዞት የአእምሮ ሥርዓቱን አፋልሶታል ማለት ይቻላል፡፡ ይህን ያልኩት ባለፈው መንፈቅ ዓመት አንዱ ቫንዳል ተሚ የታጠበበትን ቧንቧ ሳይዘጋ ሲሄድ አንድ የተባረከ ተሚ "ምነው ብትዘጋው?" ብሎ ራሱ ዘግቶት ሲሄድ ሌላኛው ቫንዳል የተባለው ወረርሽኝ በቅርቡ የያዘው የሚመስል የቫንዳሉ ጓደኛ የእርሱን ስም እየጠራ *"እከሌ'ኮ አይሰማም! መሰሚያው ጥጥ ነው!"* እያለ ሲያሞካሸው፣ እርሱም በሽታ እንደያዘው ሳያውቅ እንደ ጀብደኛ ጀነን ብሎ ሔደ፡፡ ታዲያ ይህ ሰው የአእምሮ ሥርዓቱ አልተፋለሰበትም ትላላችሁ? (ወደ ገፅ 7 ዞሯል)

(ከገፅ 6 የዞረ)

የሀገራችን የያታ ተዋፅያ (Sex Ratio) 1፡1 አካባቢ ነው፡፡ ይኸ ደግሞ 50 በሙቶ (ሊበልጥም ይችላል) የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸው ነው፡፡ ታዲያ የነዚህን ማህበረሰብ ክፍሎች እንዲህ ካሉ ገንቢ መድረኮች መጥፋት በጣም ሊያስደነግጥን ይገባል፡፡ ይኼኔ አንድ "አዝማሪ" ኮንሰርት ሊያዘጋጅ ነው ቢባል ቅንድባቸውን አበጥረው መንገዱን የሚዘጉት በብዛት ሴቶችና እነዚህ የኦፍያይዝም አብዮተኞች መሆናቸውን በያዝነው ዓመት በተደጋጋሚ ያየነው ነው፡፡ ወገኖቼ! እንዴት ነው ነገሩ? በየአመቱ በርካታ ሚሊዮኖች በሚራቡበት አህጉር ውስጥ እየተኖረ ስልኩን "አስጨምድዶ" ጃኬት ለምኖ "ኦቨር" እየተወጣ ነው "I'm Classic man" የሚባለው? ጠዋት ከሀገር ቤት ከብረት ሳይሆን "ከአፈር በተሰራ" በሚመስል አውቶቢስ የመጣ ሰው የስልኩን ጥሪ `We ride in Ferrari!'' የሚል ዘፈን ማድረጉን ምን ትሉታላችሁ? ለኔ ትንግርት ነው፡፡

በሉ ወዳጆቼ! ስለዚህ ጊቢ የትንግርት ወረርሽኝ እና በሽተኞች ልፃፍ ካልኩ ሙሉ መፅሔቱ አይበቃምና በሚከተለው ትዕምርተ ጥቁምታ ልሰናበታችሁ፡፡

"Whatever you vividly imagine, ardently desire, sincerely believe, and enthusiastically act upon must inevitably come to pass!"

- Paul J. Meyer

AFRICANS...WE MUST WAKEUP!!

ሰምንኛ ወሬዎች (ዜና)

1. *የመቐለ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ማህበር (መልሰ) ባለፈው ጥቅምት ወር ላይ ያካሔደው ምርጫ ነፃና ፍትሓዊ እንደነበር ገልፈዋ የሆነው የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ አስታወቀ፡፡ ምርጫው በህግ ትምህርት ቤት አካባቢ በጥቅምት ወር ላይ የተካሔደ ሲሆን በዚህም ምርጫ የተመረጡት አንድ ፕሬዚደንት እና ዘጠኝ የስራ አስፈፃሚ አባላት ሲሆኑ የምርጫው ውጤት በዚያው አለት ይፋ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በምርጫው ውጤት መሰረት የሦስተኛ ዓመት ተማሪው ሚኪያስ መላክ አሸናፊ ሆኗል፡፡*
   አንዳንድ ተማሪዎች የምርጫ አስፈፃሚው ጀኮሚቴ ነፃና በህግ የሚመራ ነው ብለው አያስበም ብለን ላቀረብንለት ጥያቄ ሚኪያስ መላክ "በዚህ መልኩ ምንም አይነት ብልሹ አሰራር እንደሌለና ነገር ግን አንዳንድ የሕጉደንቡ አንቀፆች ለምሳሌ ያክል የፕሬዚደንቱ የስራ ዘመን የምርጫ ሁኔታን በተመለከተ እንዲሻሻሉ ለስራ አስፈፃሚዎቹ እንደሚያስገቡ አስታውቋል፡፡ የህጉ ረቂቅም አራተኛ ዓመት በሆነው አብዱረህማን ሻሎ (ዶያሕ) አየተዘጋጀ መሆኑን እና በቅርቡም ለስራ አስፈፃሚው ቀርቦ እንደሚፀድቅ፡፡
2. *በኒቢያኖን ውስጥ አንዳንድ ተማሪዎች ተንቀሳቅሰው "ፍኖተ አእምሮ" የተባለ ማህበር እንደመሰረቱ የማህበሩ ሊቀመንበር እንዳለ መኮንን ለመፅሔቱ የዜና ክፍል አስታውቋል፡፡ የማህበሩም ተቀዳሚ አላማተማሪዎች መፅሃፍት በነፃ ተውሰው እንዲያነቡ እድል በማመቻቸት የአስተሳሰብ አድማሳቸውን እንዲያሰፉ ታስቦ የተቋቋመ መሆኑን አክለው ገልጧል፡፡ በቅርበም ይፋዊ አውደ ርዕይ (ኤግዚቢሽን) በማዘጋጀት ሰራውን በቅርቡ እንደሚጀምር ጨምረው አስታውቆናል፡፡*
3. *የሕግ ትምህርት ቤት "የሕፍ ላይፍ" ፕሮግራም ምክንያት በማድረግ በቅርቡ ወደ ባህርዳር ከተማ ትምርታዊ ጉዞ ሊያደርጉ መሆኑ ታውቋል፡፡*
4. *በመቐለ ዩኒቨርሲቲ የህግ ተማሪዎች ህብረት የኳስ ጨዋታ ውድድር በቅርቡ ሊደረግ መሆኑን የወሬ ምንጮቻችን አስታውቀውናል፡፡ ዝርዝሩን በሚቀጥለው እትም ያገኙታል፡፡*

ቆሻሻም ጨክኖ...???

© በቃለአብ ይ.

ሰሞኑን በሁሉም ሰው ዘንድ መነጋገሪ የሆነው የኛም የአፍ ማሟሻ፣ ማዘናና መቆዘሚያ ሆኖ ስለ ሰነበተው የቆሼው ጉዳይ ጥቂት ልበላችሁ፡፡ በብዙ የማህበራዊ ድረ-ገፆች ላይ እንደተገለፀው ቆሼ ተደርምሶ ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ሞቱ ሲባል ሰምታችኋል፡፡ እናም ብዙ ሰዎች "እንዴት ሰው ቆሻሻ ቦታ ይኖራል?" የሚል የግርምት ጥያቄዎችን ሲጥይቁ የተስተዋለ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ቆሼ ምን እንደሆነና፣ እንዴት እንደተፈጠረ ትንሽ ላውራችሁ፡፡

ቆሼ በአዲስ አበባ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በነፋስ ስልክ እና በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ መሀከል የሚገኝ ቦታ ሲሆን ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ የአዲስ አበባን የደረቅ ቆሻሻ ጉድ የተሸከመ ቦታ ነው፡፡ በጊዜው ማንም አይሰፍርበትም ተብሎ የተሰጠ ቦታ የነበር ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን "መሓል ከተማ" ሆኗል፣ በነዋሪዎችም ተከብቧል፡፡ እናም በዚህ የቆሻሻ መጣያ ስፍራ ለተከታታይ ዓመታት ለጤና የሚጎዱ መድኃኒቶችና ዓይነታቸው በውል የማይታወቅ ንጥረ ነገሮች ሲቃጠሉበት ቆይተዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በአካባቢው ላይ የሰፈሩ እና በአካባቢው አቅራቢያ የሚማሩ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ለረዥም ዘመናት በበሽታ ሲሰቃዩ ቆይተዋል፡፡



ሰሞኑን የደረሰው አደጋ በቆሼ ሲሆን፣ *ሰው እንዴት ይኖርበታል?* ለምትሉ ደግሞ ብዙ ሰዎች ቆሼን እንደገቢ ምንጭነት፣ እንደመኖሪያ ሥፍራነት እንዲሁም እንደምግብነትም የሚጠቀሙበት ስፍራ መሆኑን አሁን እወቁ፡፡ ምክንያቱም ከአንድ ተራ ግለሰብ ውራጅ እቃ እስከ ትልቅ ሆቴልና ተቋም የሚወጡ እቃዎችም መጣያ ስለሆነም ነው፡፡ በተጨማሪም በአሁን ወቅት ያለውን የመሬት ሽያጭ ተመን (ህገ ወጥ ቢሆንም) ማስተዋል፣ መሰል ችግሮችን በሌላ አማራጭ መንገድ እንድንመለከት ያደርገናል፡፡ እያደገ ያለው የሀገራችን ኢኪኖሚ ምንም እንኳ ፍጥነቱ ላይ ቢያጨቃጭቀንም የታችኛውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ ማድረጉ ላይ በግሌ ግልፅ አልሆነልኝም፡፡ እንደምሳሌነት የህንድን የኢኮኖሚ እድገት ጥቂት ላውራችሁ...

በአሁኑ ወቅት ከቻይናና ጃፓን ቀጥሎ የሦስተኛ የከፍተኛ ኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገበች ያለች ሀገር ስትሆን፣ የኢኮኖሚ ተንታኞች እንደሚያስቀምጡት የህንድ ሓብታም የቤቱን በር መክፈቻ በወርቅ ማሰራት የጀመረበት ጊዜ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ ለጥቀውም በጥቂት ስኩዌር ኪሎ ሜትሮች ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የመጨረሻ ደሃ ህዝቦች ተፋፍገው እንደሚኖሩ ይነግሩናል፡፡ የኛ ሀገር እርምጃስ የት ያደርሰን ይሆን?

ቆሼ በአዲስ አበባ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በነፋስ ስልክ እና በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ መሀከል የሚገኝ ቦታ ሲሆን ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ የአዲስ አበባን የደረቅ ቆሻሻ ጉድ የተሸከመ ቦታ ነው፡፡ በጊዜው ማንም አይሰፍርበትም ተብሎ የተሰጠ ቦታ የነበር ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን "መሓል ከተማ" ሆኗል፤ በነዋሪዎችም ተከብቧል፡፡ እናም በዚህ የቆሻሻ መጣያ ስፍራ ለተከታታይ ዓመታት ለጤና የሚጎዱ መድኃኒቶችና ዓይነታቸው በውል የማይታወቅ ንጥረ ነገሮች ሲቃጠሉበት ቆይተዋል፡፡

ወደ ቆሼ...

መንግስት ስለተፈጠረው የቆሻሻ መደርመስ ለሚዲያ በጠቆመው ምክንያት፣ በአካባቢው የተጀመረውን ቆሻሻን ተጠቅሞ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ለሚደረግ የግንባታ ስራ ሲሆን አደጋው የደረሰውም ለርሱ ተብሎ በተቆፈረው አፈር ቀጥሎ በሚገኘው ቦታ መኝሽራተት ነው፡፡ ይህ ፅሁፍ እስኪዘጋጅ ድረስ ባለኝ መረጃ 72 ሰዎች በአደጋው ሕይወታቸውን ሲያጡ ምናልባት ተጨማሪ አስከሬን ለማግኘት (አለ ተብሎ በአካባቢው ይታሰባልና) እስካሁን ፍሊጋው እንደቀጠለ መረጃው አለኝ፡፡ በአካባቢው የሚኖሩ እጅግ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያላቸው የእለት ጉርሳቸውን ብቻ ለማግኘት የሚተጉ ሰዎች ባብዛኛው የአደጋው ሰለባ እንደሆነም ሊታወቅ ችሏል፡፡

ለአባዛኛዎቻችን በቆሻሻ ቦታዎች መኖር የማይታሰብ ቢሆንም እነዚህን ሰዎች ግን ኑሮን ለማሸነፍ ያለውዴታቸው ተገድደው የተፈጥሮን ግዴታ ጥሰው 24 ሰዓት እንደ እሳተ ገሞራ ከሚነድደው የቆሻሻ ክምር ፊት ለፊት ለመኖር "የታደሉ" ናቸው፡፡ እንደሌላው የጋራ መኖርያ ቤቶችን ተመዝግቦ ለብዙ ዓመታት መጠበቅ የተሳናቸው፣ የቤት ኪራይ ያማረራቸው፣ አማራጭ ያልነበራው ሰዎች ናቸው፡፡ መንግስት ይህን ችግር ለመቅረፍ በተለያዩ ቦታዎች የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በብዛትና በፍትነት የገነባ፣ እየገነባ ያለ ቢሆንም አመርቂ እንዳይደለ የምንታዘበው ነው፡፡ የቤቶቹ ስርጭትና ክፍፍልም በሚመለከት ከፍተኛ ያፈፃፀም ክፍተት የሚዲያው ያንድ ሰሞን መነጋገሪያ ነበር፣ ነውም፡፡ በተጨማሪም በየጊዜው እያደገ የመጣው የመሬት ዋጋ እዚህ አካባቢ ነዋሪዎች እንኳን መሬት ገዝቶ ተከራይቶ መኖር እንዲሳናቸው አድርጓል፡፡ እንዳጠቃላይ ማንም ይመለከተኛል የሚል የትኛውም አካል የሀገራችን እድገት እውነት ሁሉንም የሕብረተሰብ ደረጃን ያመከለ ነው የሚለውን ጉዳይ ዙሮ መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡

በአደጋው ለሞቱት ወገኖች እረፍትን ለቤተሰቦቻቸው መፅናናትን እመኛለሁ!!



የትንግርት ወረርሽኝ

በአብዱረህማን ሻ. aka ደያ (abdushalo11@gmail.com)

ጥቅጥቅ ካለው የጨለማው ሕዋ ውስጥ ከሩቅ አልፎ አልፎ ብርሀንን የሚያሳዩ ነጠብጣቦች ራቅ ራቅ ብለው ይታያሉ፡፡ የግዙፉ ጨለማ መጀመሪያም ሆነ መጨረሻ አይታወቅም፣ ጥልቅ ሰፊ እና የሚያስፈራ ነው፡፡ በሰፊው አካሉም ላይ ተደላድለው የሚቁለጨለጩ የብርሀን ነጠብጣቦች ልክ እንደ ትልቅ የሐረር ሰንጋ ላይ ያሉ ጥቃቅን ተህዋሲያን፣ ምናልባትም እግሩ ላይ፣ ጭንቅላቱ ላይ ወይንም ጭራው ላይ፣ ብቻ የቱ ጋር እንደሆኑ እንኳን እንደማያውቁት እነዚያ ተህዋሲያን መኖር አለመኖራቸውንም ከቁብ ሳይቆጥር በእርጋታ እንደሚጓዘው ሠንጋ ሁሉ፣ ግዙፉ ጨለማም ተረጋግቶ ይጓዝ ወይም ይቀመጥ የማያውቁት እነዚያ ለዓይን የሚያማምሩ ለእጅ የሚያሳሱት ስስ እና ውብ የሆኑ የብርሀን ነጠብጣቦች አንዳንዴ ችምችም ሌላ ጊዜ ራቅ ራቅ ብለው መጀመሪያው በውል የማይታወቅ ዘመን ጀምሮ ይቁለጨለጫሉ መጨረሻው እስከማይታወቅ የዘመን ጥግ ድረስ፡፡

ይህን ሁሉ ቸል ያለው "ግዑዙ" ጊዜም ሁሉን ተሸክሞ ወደፊት ይነጉዳል፡፡ "ባቡሩ" ጊዜ እግረ መንገዱን በሕዋው ላይ ከሚገኙ ጥቃቅን የብርሀን ነጠብጣቦች አንዷ የሆነችውን ክብ እሳት ፍም ከብበው ከሚዞሩት ትልልቅ 9 አለሎዎች ቆንጆዋ የውሓ አለሎ ጥሎኝ ጉዞውን ቀጠለ፡፡ አዎን! የሠዎች፣ የእፅዋት፣ አሣዎች እና ሌሎችም ፍጥረታት ሁሉ ቤት፣ ምድር፡፡ ከፀሐይ በታች ሰዎች(ምእራባዊኑ/ነጮች) ገዥ በሆኑባት ሰማያዊ አለሎ፡፡ የሠዎቹ(የነጮቹ) ገዥነትም በጠንካራ አለት ላይ የተገነባ ፍጥረትም የማይነቀንቀው ዘመን ተሻጋሪ ኃይልና ጠንካራ ሆነ፡፡

ከዚያ በፊት እንዲህ ነበር የሆነው...

በጥንቱ ዘመን የሠው ልጅ ኑሮ እንደዛሬው ሳይሆን የወባ ትንኞች ሕይወት ማጥፋት የሚችሉ አደገኛ እና አስበርጋጊ የነበሩበት ጊዜ ነበር፡፡ ውኃ ወለድ በሽታዎች ከጅምላ ጨራሽ አቶሚክ እና ኬሚካላዊ መሳሪያ ያልተናነሰ ጥፋት የሚያስከትሉበት፣ እንስሳትና እፅዋት ባልታወቀ ምክንያት ክው ብለው የሚደርቁበት የጨለማው ዘመን....፡፡ ባለብሩህ አእምሮ ባለቤት ሰውም ይህንን አስፈሪ ዘመን ከአካባቢው ድራሹን ለማጥፋት ጦር መሳል፣ ጋሻ መቀጥቀጥ፣ አጋሰስ እና ፈረስ መጫን አላስፈለገውም፡፡ ለጥያቄው መልስ ያገኘ ዘንድ በርትቶ መረመረ፣ የምርምሩ ውጤት የሆነውን ጥበብና እውቀት እንደጦር እና ጋሻ ታጥቆ ተነሳ(ENLIGHTENMENT እና RENAISSANCE'ን ልብ በሉ) ፡፡ የአስፈሪው ዘመን የጡት ልጆች የሆኑትን በሽታ፣ ርሃብ እና ችነፈር ሽምጥ ቁልቁል ጋለቡ፡፡ መኖር ወደሚችሉበት እና በትንግርት በሽታ ወደ ተወረሩት የጥቁር ሕዝቦች ምድር አፍሪቃ መጡ፡፡ በዚያም የድንቁርናን ካባ ደርበው የመሓይምነት አክሊል የደፉ ታላላቅና ታናናሽ ነገስታት እንደበግ መንጋ የሚነዱላቸውን ሕዝቦች በአስተሳሰብ አድማሳቸው ልክ በነገሱበት ጠባብ ቤተ-መንግስት በራስ ወዳድነት አልጋ ላይ ጋደም ብለውና በማን አለብኝነት ዙፋናቸው ላይ ተዘርፍጠው መንጋውን ለረጅም ዘመን ሲነዱት ኖረዋል....፡፡(ሙጋቢ/ኢዲአሚን/ጋዳፊ/ኡመር/ያህያ ጃሚ/የቀድሞው መንግስቱ/ ኢሳያስ/ ዚያድ ባሪ.....)

ዘር፣ ቦታ እና ጊዜ የማይለየው ፈሪሃ ጥበብ እና እውቀት የሆነው የጨለማ ዘመንም የነገስታት ንጉስ ሆኖ በሰፊውና በመንጋው ሕዝብ ላይ የጡት ልጆቹን ድህነት፣ ረሃብ፣ ችነፈር፣ ልዑላን እና ልዕልት አድርጎ በመሾም ሰጥ ለጥ አድርጎ ይገዛል፡፡ እዚህም(አፍሪካ) በተመሳሳይ መንገድ እስኪባረር ፀሐይ በማትጠልቅበት ሰፊ ግዛቱ ተደላድሎ ይኖራል፡፡ በሌላ በኩል የጨለማውን ዘመን እንደጦስ ዶሮ ከነግሳንግሱ ከላያቸው አዙረው የጣሉት ሰዎች(ምእራባዊያኑ) ድላቸውን በዘፈን፣ በሽለላ እና ቀረርቶ ለማጣጣም ጦርና ጋሻቸው የሆነውን ጥበብ እና እውቀት በየግድግዳቸው ላይ ሰቅለው ድግስ ደግሰው፣ ፍሪዳ ጥለው፣ እሳት ከብበው አልጨፈሩም፡፡

...በዚያም የድንቁርናን ካባ ደርበው የመሓይምነት አክሊል የደፉ ታላላቅና ታናናሽ ነገስታት እንደበግ መንጋ የሚነዱላቸውን ሕዝቦች በአስተሳሰብ አድማሳቸው ልክ. በገነቡት ጠባብ ቤተ-መንግስት በራስ ወዳድነት አልጋ ላይ ጋደም ብለውና በማን አለብኝነት ዙፋናቸው ላይ ተዘርፍጠው መንጋውን ለረጅም ዘመን ሲነዱት ኖረዋል

በጭራሽ! እንዲያውም የማያባራ ጥያቄ በመጠየቅ ጥልቅ ምርምር በማድረግ ከዚያ የሚያገኙት እውቀትና ጥበብ እንደ ዝናር በመታጠቅ ወደፊት አሉ፡፡ ተተኪው ትውልድም ***"የጥበብ መጀመሪያ መጠየቅና መመራመር ነው፡፡"*** የሚለውንም ጥቅስ በልቡ አትሞ ተከተለ፡፡ ለሁለቱም የሰው ዘሮች የማያዳላው የዘመን ቁጥርም 21ኛው ክፍለ ዘመን ደርሷል፡፡ ለእኛም ታሪክ የመስራት፣ የመጻፍ ወይም የማውራት አማራጮችን ጠረጴዛ ላይ ደርድሮ ይታዘባል፡፡

ታዲያ በእኔ እድሜ ከማስታውሰው ታላላቅ ኹነቶች አንዱ እዚሁ አዲ-ሓቂ ጊቢ እያለሁ ባለፈው ዓመት የተከሰተ ነው፡፡ የጨለማው ዘመን ልዑሉ ረሃብ በአባቱ ግዞት ከሚኖሩ 15 ሚሊዮን መንጋ ሕዝቦች ላይ ጭካኔ በተሞላበት መልኩ ጅራፉን አሳረፈ፡፡ ቅጣቱም ሞትን የሚያስንቅ አሳማሚና አስከፊ መሆኑን ለመገንዘብ አፍሪካ መኖር ከበቂ በላይ ነው፡፡ የ15 ሚሊዮኑን ሆድ የሌሎቻችን ልብ ረሃብ ጠብሶ አለፈ፡፡ ኹነቱ ሲፈጠር በነበርኩበት አዲ-ሓቂ ጊቢም ትንግርት የሚባል ወረርሽኝ ክፉኛ ተንሰራፍቶ ነበር፡፡ ያታ፣ የትምህርት ክፍልና እድሜ ሳይለይ ብዙዎችን አጠቃ፡፡

ይህ በሽታ በሰው ውጫዊ አካል ላይ ምንም ጉዳት የማያደርስ ሆኖ አእምሮን ክፉኛ በማጥቃት ግራ የሚያጋቡ፣ ኢ-ምክንያታዊ ሃሳብ ባለቤት፣ ይሉኝታን ሰርቆ አስመሳይ፣ ብሎም የአርቲ ቡርቲ ሃሳቦች መከማቻ፣ ቆሞ የሚሄድ ስልቻ ያደርጋል፡፡ ይህ የመጀመሪያው ምልክቱ ሲሆን፣ **የትንግርት በሽታ የመጨረሻው ደረጃ ሲደርስ ቤተ-መፅሃፍት የሚያህል ቤት ውስጥ ያፀዳዳል፡፡** የዚህ በሽታ ተጠቂዎች የሚሰሩት፣ የሚያስቡትና የሚያወሩት ነገር በጠቅላላ ጉድ የሚያሰኝ ሆኖ ሳለ ለራሳቸው ግን ፍፁም ጤነኛና እውነት ሆኖ ይሰማቸዋል፡፡ በሽታ አይደል?

ቀጥዬ አለፍ አለፍ እያልኩ ስለነዚህ በሽተኞች ሥራ፣ አስተሳሰብ፣ የሕይወት ፍልስፍና እና አጠቃላይ ሁኔታ ነካ ነካ

እያደረግሁ ለማስቃኘት እሞክራለሁ... ነካ ነካ ማድረጌ ከበሽታው በስፋት መዛመት፣ ከበሽተኞቹ ቁጥር ጣራ መንካት እና ከበሽታው ደረጃ መለያየት አንፃር በዚህ ፅሁፍ ብቻ ሊዳሰስ አለመቻሉ ነው።።

<u>ማሳያ 1</u>

ወዳጄ ነው።። ልክ እንደ ሰፊው ሕዝብ ሁሉ ገበሬ ከሆኑ ወላጆቹ የተወለደ ሲሆን እዚህ ጊቢ መጥቶ ተምሮ ተመራምሮ፣ ዝቅ ሲል እነዚህን ምስኪን ቤተሰቦቹን ከፍ ሲል ልክ እንደቤተሰቡ ሁሉ በጨለማው ዘመን ድህንነት እና ኋላቀርነት ቀንበር ስር የሚማቅቁ አፍሪካዊያን ሚሊዮን ቤተሰቦችን ከዚህ በሚታጠቀው ቁንፅል እውቀትና ጥበብ ነፃ ሊያወጣ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጦ የመጣ መሆኑን አስታውሳለሁ።። ታዲያ ይህ ወዳጄ በ2006 ዓ.ም በአቧራ ከተለወሰው አውቶቢስ መኪና ለመጀመሪያ ጊዜ የመቸለን መሬት ሲረግጥ "ኩርቱ ፌስታል ሙሉ ልብስ" እና "ሻንጣ ሙሉ በለ" ጀርባው ላይ ጣል አድርጎ ነበር።። በርግጥ ይህ ምንም ማለት አይደለም።። እንደ አፍሪካዊ ብሎም እንደ ኢትዲያዊ አማካይ ዜጋ ይህ ብዙም ተጋንኖ ሊወራ የሚችል አይደለም።። በነገራችን ላይ ተወደደም ተጠላም ሁሉም ኢትዲጲያዊ የማያታይ ግን አብሮት የሚወለድ መንታ ወንድም አለው።። ድህነት!! ደሃ ለመሆን የደሃ አገር ዜጋ መሆን በቂ ነውና...።።

ይህ ወዳጄ በመማ ባሙቱ በግቢው ክፉኛ ተንሰራፍቶ በነበረው የትንግርት ወረርሽኝ ተለከፈ።። እርግጥ ነው አላንቀጠቀጠውም።። ብርድ ብርድ ብሎትም ተጠቅልሎ አልተኛም።። ትኩሳትና ሳልም አልታየበት።። እነዚህ ሁሉ የትንግርት በሽታ ምልክቶች አይደሉም።። ግና የሚያስበው፣ የሚያወራው እና የሚያልመው ሁሉ የእርሱን የኋላ ታሪክ ለሚያውቅ ብሎም ለጤነኛ አእምሮ ባለቤት ለሆነ ሁሉ ጉድ የሚያሰኝ ነበር።። ለእርሱና መሰል የበሽታው ተጠቂ ጓደኞቹ ግን ትክክልና ተገቢም ነበር።። ምልክቶቹም በግልፅ መታየት ጀመሩ።። *"ነን ካፌ መሆን አለብኝ።። ያውም ውጪ ሶንትራት ካልያገዙ ሞቼ እገኛለሁ።።"* የምትል ነጠላ ዜማ አውጥቶ አንድ ሰሞን ሲዘፍን ቆየ።። በዚያው ሰሞን *Come on, come on, turn the Radio on It is Friday night...* የሚለውን የSiaን ዘፈን በሰኞ ምድር ከቀዝቃዛ ጠላው ጋር ሲኮመኩም ያመሸና በሞቅታ እንዳለ ፀሃሽ ሱቅ አካባቢ ተገናኘን።። ከመጣበት ማህበረሰብ የተጫኑበት እልፍ አእላፍ ተስፋ፣ ኃላፊነትና ልማድ በበሽታውና በፍቃዱ ተንጠባጥበው አልቀው ኖሮ በመጨረሻዋና ልትለቀው ባልቻለችው የረኽም የሰላምታ ዘዬው ተቀበለኝና ጊዜ ሳያጠፋ በሕይወቱ በጣም አሳሳቢ እና ወሳኝ ጉዳይ እንደገጠመው አስረግጦ ነገረኝ።። "ስማ..." እየተንተባተበ የማውቃትን ሴት ስም ጠርቶ "አወካት?... ሶስተኛ ዓመት ነኝ (ተቆጣ) ...እ እ እ... አወካት...ዑ! ዑ! ዑ!... በናትህ ሰመጠችልኝ እኮ... ይኼ ፎንቃ... እየው በናትህ ፎቶዎቿን" የስልኩን "ፓተርን" ከፍቶ "My Life" በማለት ከሰየመው ሳጥን ውስጥ ከማህበራዊ ድረ-ገፅ ያወረዳቸውን ፎቶዎቿን ፈጠን ፈጠን እያለ ያሳየኝ ጀመር።። አፏን አሞጥሙጣ ለብቻዋ የተነሰችው "ሰልፊ"፣ ወደ ፊት ፈንደድ ብላ... ደማቅ ቀይ የከንፈር ቀለም ተቀብታ "ደም ልሳ ከቁራ የወጣች ድመት" መስላ ከሌሎች ሁለት ጓደኞቿ ጋር የተነሳችውን ሌላ "ሰልፊ".. እያሳየኝ... "በናትህ ምትገርም እኮ ናት!" አለኝ ስልኩን ኪሱ እየመለሰ... ከሌላ ኪሱ ወረቀት እያወጣ "ይነቅሳል ሚባለውን አርት ተማሪ ታውቀዋለህ?" አለኝ ወረቀቱን እየሰጠኝ... ሁለት የላቲን ፊደሎች የተደጋገፉ የሚመስሉ የተሳለበት ነበር ወረቀቱ።። በሃሳብ ወደ'ኋ ሄድኩኝ... "ከፊኋ የተጣላች"፣ በጣም የሚያማምሩ ወደ ሶስት የሚጠጉ የተለያዩ የፊረስ ጭራዎችን በራስ "ቅኋ" ላይ ጎዝጉዛ የምትሄድ የእለት ጉርሿ ምንጭ እስኪመስለኝ ማህበራዊ ሚዲያ ላይ ተጥዳ የምትውል፣ ትምህርት ሚኒስትር መቸለ ዩኑቨርሲቲ ሳይሆን "ፎቶ ደስታ" የላካት ይመስል የማህበራዊ ድረ-ገፁን በፎቶ ማዕበል የምትንጥ ሌላ የትንግርት በሽታ ተጠቂ .....።።

ለወዳጄ ከልቤ ደነገጥኩለት።። 80% ከሚሆነው የራሱንና የቤተሰቡን የምግብ ዋስትና እንኳን ማረጋገጥ አቅቶት በ10 እና 15 ዓመታት ልዩነት በረሃብ አለንጋ ከሚገረፈው ገበሬ አካባቢ አንዱ ነዋሪ ለሆኑት ቤተሰቦቹ ደግሞ የበለጠ ብርክ ያዘኝ።። "የነን ምግብ ቤተሰብ ልጅ ነን ካፌ ለመሆን ሲጨነቅና ሲጠበብ ማየት" ትንግርት ነው!!

ማሳያ 2

ዓለም ላይ የፖፕ ባህል (Pop culture) መስፋፋትን ተከትሎ "እንኳን ዘንቦብሽ" የሆነው ሕዝባችን በተለይም ወጣቱ በዚህ ባህል ክፉኛ መዋለቅለቁን ለማስተዋል ሩቅ መሔድ ሳያስፈልግ እዚሁ ጊቢያችን ውስጥ ቆም ብሎ ማየት ከበቂ በላይ ነው።።

<u>"ኮፍያይዝም"</u>፣ በተለይ በያዝነው ዓመት የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት መጠናቀቂያ አካባቢ የጊቢያችን ሴቶች ዩኒፎርም እስኪመስል ድረስ ሴቱ ሁሉ ረዘም ያለ ጋዋን አንገርግጎ ሲዞር ማየት አዲስ ትዕይንት ነበር።። ነገሩን በደንብ ያጤነ ፈዘኛ ጓደኛዬ "... ይኸን የሰሞኑን «ጋዋኒዝም» የሴቶች አብዮት በ`ጥቁር ፍቅር` ሴት ተዋናይ `ኤሊፍ` ላይ የታየ ነው።።..." ሲል አመጣጡን ከገለፀ በኋላ "ምነው ይኸች ኤሊፍ አንድ ቀን በደረቷ እተሳበች ብትሔድና የዚህን ጊቢ ሴት ባየሁት..." ከማለቱ ሌላው ቧልተኛ አፈፍ ብሎ "ወዳጄ... ጊቢውን የአባብ ዩኒቨርሲቲ ልታስመስለው ነው'ንዴ?" ብሎ በነገሩ ላይ የፈጠረብን ፈገግታ ሳይደበዝዝ "ኮፍያይዝም" ብለን *"ዮተፃዋንበት"* ስልተ አለባባስ ተከተለ።። እሱ ደግሞ *ሄኔድሪክ ሌማር* እና *ጀስቲን ቢበር* ከተባሉ ሙዚቀኞች ነው የተኮረጁው አለ።።

እኔ በበኩሌ ከኮፍያውያን (ከኮፍያ አብዮተኞች) *ጋር* ችግር የለብኝም።። ጭንቅላታቸው ላይ አይደለም ቆብ ሰፈድ ቢያደርጉ የነርሱ ምርጫ ነው።። ግን እነዚህ ወዳጆቻችን ምን ያህል "አሳቢ" (Thinker) ናቸው? የሚለው ለወደፊቱ የሀገራችን እጣ ፈንታም ወሳኝ ስለሆነ እርሱ ላይ ጥቂት ነገር ብንባባል... አንድ ሰው "አሳቢ"(Thinker) ነው ማለት ስለቁርስ፣ ምሳ፣ እራቱን... ከዚያ ስለመጠጥ፣ ሲጋራውና... ስለ "ሥሪያው" ... ስለ ትምህርቱና ስለ ጥናት "እንደነገሩ"...ማስኬድና ማሰቡ አሳቢ አያሰኘውም።። ነገር ግን አጠቃላይ ስለማህበረሰቡ ያለውን ግንዛቤ ከፍ ለሚያደርጉ ነገሮች ጊዜውን ሰጥቶ፣ ሰውቶ ያነብባል፣ ያጠናል፣ ምልከታዎችን ያደርጋል፣ ይመረምራል? ሃሳብ ያመነጫል? ለሚሉት ጥያቄዎች እኔ በበኩሌ አነዚህ ወገኖች መርቅነው "ካንዲ ክራሽ" ሲደረምሱ ስለቅዳሜ "ጨብሲ" እንጥላቸው እስኪያብጥ በኩራት ሲያወሩ ከመስማትና ከማየት ውጭ...ብዙዎቹ አሳቢ ባለፈበት አላለፉም


አሁን ሰሞኑን እንኳ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴን የሚያክሉ የሀገራችን ታሪክ ፀሃፊ መጥተው ባደረጉት *ፖብሊክ ሌክቸር* ላይ ላመል እንኳን አልመጡም ማለት ይቻላል።። በተለይ የሴቶቹ ቁጥር ለታዘበ በጣም አስደንጋጭ ነበር።። (ወደ ገፅ 3 ዞሯል)

(ከገፅ..3 የዞረ)

የበለጠ የሚያሳዝነው *"እኔ ምን አገባኝ?"* በሚል ገዳይና ገደል ከታች ብሂል እየታገዝን እንደዚህ የሚያደርጉ ቫንዳል ተማሪዎችን እያየን "ላሽ" እንላለን፡፡ ለምን? ወገኖቼ ይህ ንብረት የጋራችን ሆኖ ሳለ መከላከል እንኳ ቢያቅተን ድርጊቱ ተገቢ እንዳልሆነ እንዴት አስተያየት ሰጥቶ ማለፍ ያቅተናል? ይህ ፊዕሞ "ፋርነት" እንዳይደል እንዴት አጣነው? ይህ ስልጡን ሰው መሆን ይመስልኛል፡፡ ንብረት ሲጠፋ፣ አላግባብ ሲወድም ስናይ ማስተማርና መናገር ምክንያትዊ መሆን ይመስለኛል፡፡ እርግጥ አንድ ሰው ሳያውቅ አንድን ንብረት ወይም መገልገያ ባለማወቅ ሊያጠፋው ወይም ሊበላሸው ይችላል፣ የእኔ ወቀሳ ግን ተመሳሳይ ድርጊት እያወቁ ወይም በከፍተኛ ቸልተኝነት ቧንቧ ክፍት ለሚተዉ ሽንት ቤት ዳር "ለሚጠቀሙ"፣ ባኞ ቤት ለሚዐዳዱ፣ መፅሃፍ ላይ ለሚፅፉና ገፅ የሚቀዱ ናቸው ቫንዳል ብዬ የምጠራቸው ፡፡ እነርሱ ናቸው የጋራ ንብረቶቻችን አውዳሚዎች፡፡



ሲመስለኝ ብዙዎቻችን ተሜዎች እዚህ ጊቢ ከመምጣታችን በፊት ዩኒቨርሲቲ ስንባል እንዲህ ያለ አካባቢ ጠብቀን አልመጣንም ነበር፡፡ *(በፅዳታቸውና በውበታቸው ሊደነቁ የሚችሉ ካምፓሶች እንዳሉ ልብ ይሏል)* የመማሪያ ስፍራው ማራኪ፣ የመመገቢያ አዳራሾች ጤናማ ሽታ ያላቸው፣ የመኖሪያ ሕንፃዎቹ የተጠበቁ ብቻ ባጠቃላይ ለጤናም ለደሕንነትም ምቹ እንደሆኑ ይሰማን የነበር ይመስለኛል፡፡ ተማሪዎችም መብትና ግዴታቸውን የሚያውቁ ምን፣ የት፣ መቼ እና እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው የሚገነዘቡ እየመሰለን



እዚህ እንደመጣን እገምታለሁ፡፡ አንዳንዱ አንድ ሁለት ሳምንት አይቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ፣ አብዛኛው በዚህ ሁኔታ ውስጥም ቢሆን እየተቸገረ ይማራል፣ ተምሮም ይመረቃል፡፡ ለዚህ የቫንዳሎች የጥፋት ዘመቻ መፍትሄ ብሎ ነገር የሌለ ይመስል፣ የጊቢው አስተዳደርም ታዛቢ ሆኖ አንድ በርታ ያለ ሕግ አለማውጣቱም ሌላው ግሩም ጉዳይ ነው የሚሆንብኝ፡፡

አንድ Environmental club የሚባል ክበብ የተቋቋመ ቢሆንም፣ *"የራሷ እያረረባት የሰው ታማስላለች"* እንደሚባለው ተረት፣ የጊቢያችን "ጉዶችን" ማስተማር ሲኖርባቸው *"የመቐለን ትምህርት ቤቶች እየዞርን አስተማርን"* ይላሉ፡፡ አንዳንዱም የፅዳት ዘመቻ እያለ የዋና ዋና መንገዶች ተከትሎ ያለውን ትንሽ ቆሻሻ ነካክቶ ተቀረውን እንደክፉ ጎረቤት ደጀፍ ይተወዋል፡፡ ከዚህ በፊት እንደሰማሁት አንድ የሕግ ትምህርት ቤት መምህርም ትንሽ ተንቀሳቅሶ በምን ምክንያት እንደሆነ ባላውቅም አሁን ሲንቀሳቀስ አይሰማም፡፡ ሌላውማ አማርሮ ሲያወራ እንኳ ሰማሁ የሚል የለም፡፡

እኔ ምለው! ይህ ጊቢ እኮ እኛ እስካለን ድረስ የኛ የሁላችንም ነው፡፡ ለምንድነው ትንሽ እንኳ ቁብ የማይሰጠን? ጥቅሙም ጉዳቱም ለየራሳችን ነው እኮ፡፡ ዩኒቨርሲቲው እንደሆነ በር ተሰበረ፣ መስኮት ተሰበረ እያለ በሚወስደው ገንዘብ እንኳን ጥገና ሌላ አሰርቶ አይተን አናውቅም፡፡ *እዚህ ነገር ላይ ጆሮ የለንም* የሚል ነው የሚመስለው፡፡ ታዲያ እኛ ራሳችን ለምን አንቋቋምም፣ ለምን ሓላፊነታችንን መወጣት ተሳነን? እስከመቼ ነው ዩኒቨርሲቲያችን ባለቤት ያጣ የሚመስለው? የዕውቀት ቤታችን እኮ ነው! ይህን ቦታ "ገማሞ" ካልሆነ በቀር ዩኒቨርሲቲ ብለን መጥራት እየከበደን እኮ ነው፡፡ ለመኖሪያችን እንደራሳችን ቤት ለምን አንጠነቀቅለትም? ሁላችንም ቫንዳል ብንሆንም ለመለወጥ ሓላፊነታችንን ባግባቡ ለመወጣት ቆርጠን እንነሳ፡፡ ለሚመጡት ታናናሾቻችን አርአያ እንሁን፡፡ ይህን ጎጂና ፀያፍ ድርጊታችንን ላፍታ ቆም ብለን እናስበውና ለለውጥ እንዘጋጅ፡፡ ታሪኩን የሚለውጥ ትውልድ አካል ሆነን ታሪክ እንስራ፡፡ በሌላ ርዕሰ-ጉዳይ እስክንገናኝ በዚህ ቁም ነገር አዘል የአንስታይን ጥቅስ ልሰናበታችሁ...

"The world is not be destroyed by those who do evil, but by those who do watch them without doing anything."

ቸር እንሰንብት!



በሃሽን ሀ.

ወንድም/እህት የወደቀን እቃ አግኝተህ/ሽ ታውቃለህ/ሽ? ከዚያስ ምን አደረግኸው/ሽው? ተጠቀምክበት/ሽበት? ወይስ ለባለቤቱ መለስከው/ሽው?

በህይወታችን፣ በኑሯችን ውስጥ በተለያዩ መንገዶች እቃ ይጠፋብናል፣ የጠፋም ወይም የወደቀም እናገኛለን፡፡ በዚህ ረገድ ያለን አስተሳሰብ ምን ይመስላል? ወድቆ ያገኘነውን ንብረት ለባለቤቱ መመለስ ይገባናል ብላችሁ ታስባላችሁ? ባህላችን፣ እምነታችን እና ሕጋችን ምን ያላሉ? አብረን እንቃኘው?

በዚህ ጉዳይ ላይ ሁላችንም የየራሳችን ሃሳብ እናራምዳለን፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ገብቱን በጥልቀት ስናየው መዐት ሃሳቦች ይፈስሳሉ፣ ይጎርፋሉ፣ ይሰነዘራሉ፣ ይወራሉ፡፡ እነዚህን ሃሳቦች ጠቅለል አድርገን በሁለት ልንከፍላቸው እንችላልን፡፡ እነርሱም የእድል ሃሳብና የሰራ ሃሳብ ናቸው፡፡

የመጀመሪያ የእድል ፅንሰ ሃሳብ አራማጆች እንደሚሉት *“የወደቀን ንብረት(እቃ) አግኝተህ ለራስህ ጥቅም ልታውለው ይገባል፣ እድል ላንተ አጭታሃለች፡፡ ስለዚህ ይህንን እድል መጠቀም ይኖርብሃል”* ይላሉ፡፡ ምክንያታቸውን ሲያስቀምጡ፣ *“እኛ ሰዎች በዚህች ምድር እሰካለን እቃ ይጠፋብናል፣ በዚያው ልክ እቃ እናገኛለን፡፡ እናም እቃ ማግኘትና ማጥፋት የህይወታችን አንድ አካል ነው፡፡ ይህንን እውነታ ልንቀይረውም፣ ልንክደውም፣ ልንለውጠውም አንችልም፡፡ ስለዚህ የጠፋውን/የወደቀውን አግኝተህ መጠቀም ተገቢም፣ ትክክልም ፍትሓዊም ነው፡፡በኑሯችን ውስጥ እቃ መጣል/ማጥፋት እቃ እንደተሸጠ፣ እቃ ማግኘትም እንደመግዛት ተቆጥሮ መታየት አለበት”* ይላሉ፡፡ ምክንያቱም ከዚህ እውነታ ማፈንገጥ አለመቻላችን እንዲሁም በልምድ ደማችን ውስጥ የገባ የእኛ የሰዎች ሁነኛ መመሪያችን ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የመጠቀም/የባለቤትነት መብታችን ፍፁም አይደለም በማለት 3 ልዩ ሁኔታዎችን ያስቀምጣሉ፡፡ እነርሱም፡

1. የእቃውን ባለቤት የምናውቀው ከሆነ
2. ባለቤቱ እቃውን ተቸግሮ እየፈለገ ከሆነ
3. ባለቤቱ እቃውን እንደጠፋው በተለያየ መንገድ ማስታወቂያ ካወጣ ወይም ካስነገረ

ስለዚህ የእድል ሓሳብ ደጋፊዎች የሚያነሱት እነዚህን ምክንያቶች(ልዩ ሁኔታዎች) በሚቃረን መነገድ መጠቀም እንደሌለብን ነው፡፡ ምክንያታቸውን ሲገልፁ አንደኛው ሰው እቃውን ተቸግሮ የሚፈልግው ወይም ማስታወቂያ የሚያወጣው የጠፋበት ንብረት በህይወቱ ወሳኝ ስለሆነ ተብሎ ነው የሚገመተው፡፡ ወሳኝነቱ ኢኮኖሚያዊ ወይም ሌላ (ስጦታ፣ ትዝታ ወዘተ...) ሲሆን ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት የሚያነሱት ባለቤቱን የምታውቀው ከሆነ የሚል ዕይታን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ይህንንም ሲገልፁት መተባበር፣ መተሳሰብ እና መተማመን በማህበረሰቡ ዘንድ እንዲሰፍን ከሚፈለግበት አንጻር ነው፡፡ ሃሳባቸውን በጥቅልሉ ስናየው ከእነዚህ ከሶስቱ ልዩ ሁኔታዎች ውጭ የተገኘን ንብረት መመለስ የፈጣሪን ስጦታ በግልፅ እንዳለመቀበል ያሳስቡታል፡፡

ሁለተኛው ፅንሰ ሃሳብ ማለትም የ*ሥራ* ሃሳብ አራማጆች እንደሚሉት ደግሞ *“እቃ ማጥፋት እና ማግኘት ለሕይወታችን ያለ ቢሆንማ እቃ በማግኘትህ ብቻ መጠቀም ግን የሰውን ሳብ፣ ጉልበት እና እውቀት ገደል ማስገባት ነው፡፡ ስለዚህ የወደቀውን አግኝተህ መጠቀም ሳይሆን ለሚመለከተው (ተወካይ፣ እናት፣ አባት፣ እህት፣ ወንድም) ውይም ለባለቤቱ ለራሱ መመለስ ነው የሚገባህ”* ይላሉ፡፡ አንድ ሰው እቃ በማግኘቱ ብቻ ይጠቀም ካልን የስራ አስፈላጊነትን ዋጋ እንደማሳጣት ነው፡፡ በዋነኝነት ደግሞ “የሠራ ያገኛል” የሚለውን ትልቅ የእድገት ፅንሰ-ሃሳብ ይቃረናል፡፡ ሃሳባቸውን ሲደመድሙ እንዲህ ይላሉ፡- *በሆነ መንገድ ሳብን፣ እውቀትን አፍስሶ ጥሮ ግሮ ንብረቱን ያፈራው መጠቀም አለበት፡፡”*

ውድና የተከበራችሁ የዚህ አምድ አንባብያን፣ ከሁለቱም ፅንሰ ሃሳብ የተሻለና አሳማኝ የሚመስለው የትኛው ነው? የእድል ወይስ የስራ? ሙግታችሁን ከራሳችሁ ጋር ቀጥሉ... በዚህ ጉዳይ ላይ

[redacted]

ሕጋችን ምን ይላል? ቀጣይ ምልከታችን ነው፡፡

ፍትሐ-ብሔር ህግ አንቀፅ 1154

(1) ግዙፍነት ያለውን አንድ ተንቀሳቃሽ ነገር ያገኘና እጅ ያደረገው ሰው ያገኘውን ነገር እንዲያስታውቅ የሚያዝዘውን የአስተዳደር ደንብ መፈፀም አለበት፡፡

(2) እንደዚህ ያለ ደንብ የሌለ እንደሆነ የተገኘው ነገር ግልፅ እንዲወጣ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ሁሉ መፈፀምና ያገኘውን ነገር ባለ ሓብት ለሆነው ሰው ለማስታወቅ እንደነገሩ ሁኔቴ የታዘዘውን ምርመራ ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡

ይህ አንቀፅ የሚያሳየን አንድ ሰው የጠፋ እቃ ካገኘ እቃውን በይዞታው በማድረግ አስተዳደር ሕግ ካለ በዚያ ከሌለ ደግሞ ባለቤቱ ሊገኝ በሚችልበት ቦታ ራሱ ማስታወቂያ በማውጣት ግዴታውን መወጣት አለበት፡፡ በልምድ ግን፣ እቃ ካገኘን እቃውን ይዘን ፖሊስ ጣቢያ፣ ማዘጋጃ ቤት እንወስዳለን፡፡ ሕጉ ይህም መሰል ግዴታ አልጣለብንም፡፡ እቃውን በራሳችን ይዞታ ይዘን ማስታወቂያ ካስነገርን በቂ እንደሆነ ነው የሚያሳየን፡፡ ከአንቀፅ 1154-1158 የፍትሐ-ብሔሩን ድንጋጌዎች ጠቅለል ባለ መልኩ ስናያቸው እቃውን ያገኘው ሰው ግዴታውን ከተወጣ መሸለም እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች ከአንቀፅ 1192 ጋር አጣምረን ስናየው ሁለት ነገሮችን እናገኛለን፡፡

1. እቃ ያገኘው ሰው እቃ ባለቤቱ እስከሚገኝ ድረስ እቃውን ለ10 ዓመታት ይዞ እንዲቆይ
2. የእቃውን ባለቤት በ10 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ካልተገኘ ወይም መመጣት ካልቻለ እየፈለገው አይደለም በሚል ግምት ያገኘው ሰው የባለቤትነት መብት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የወንጀለኛ መቅጫ ህጋችን አንቀፅ 680(1) የተገኘውን እቃ በጊዜው ማስታወቂያ ሳታስነግር ዝም ብለህ መጠቀም/በይዞታ ማድረግ በእስራት እና በገንዘብ ሊያስቀጣ እንደሚችል ይገልፃል፡፡

ከእነዚህ የሕግ አንቀፆች እንደምንረዳው ሕጉን ታሳቢ አድርገው ማህበረሰቡን ሊቀርፁበት የፈለጉበት አስተሳሰብ፣ ሰዎች እቃ አግኝተው ባለቤቱን ለማግኘት በህጉ መሰረት ወይም ሚዛናዊ የሆነ ጥረት አድርገው ባለቤቱን ሊገኝበት በሚችል ሁኔታ ማስታወቅ እንዳለት ነው፡፡ ነገር ግን ሕጉ ይህን ግዴታ ሲጥልብን ኪሳራችንን እና ውጪታችንን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በአጠቃላይ እቃ ያገኘው

ሰው ይህንን ግዴታውን ከተወጣ በኋላ የጠፋበት ሰው እስኪመጣ ድረስ በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ድረስ ይዞት ሊቆይ ይችላል፡፡ የጠፋበት ሰው በዚህ ጊዜ ካልመጣ በይርጋ ዘመን ምክንያት የባለቤትነት መብቱን ያጣል፡፡ በዚህም መሰረት እቃውን ያገኘው ሰው የእቃው ባለቤት ይሆናል ማለት ነው፡፡

የአጠቃላይ የሕጉ አረዳድ፣ አንድ ሰው የጠፋ/የወደቀ እቃ በማግኘቱ ብቻ የእቃው ባለቤት ሊሆን እንደማይችል ማሳየት ነው፡፡ የሰውን ላብ፣ ጉልበት፣ እውቀት በ"እድል" ብቻ ሊወሰድ አይቻልም፡፡ በተጨማሪም በተቀመጠው ድንጋጌ መሰረትም ባለቤት ሊኮን የሚቻልበት መንገድ እንዳለ መረዳት ችለናል፡፡ ምንም እንኳ ህጉ የስራ ፅንሰ-ሃሳብን የሚያራምድ ቢመስልም የእድል ፅንሰ-ሃሳብም ቦታ አልተነሳውም፡፡ የተራዘመ ጥምረት አለው ማለት ይቻላል፡፡ ይህንንም ያደረገው ቸልተኛ የእቃ ባለቤት እንዳይኖር ታስቦ በማድረግ ይመስላል፡፡ መልካም ጊዜ!

(ከገፅ 10 የዞረ)

ለምን አናነብብም?

ለዚህ መሰሉ ጥያቄ መልስ መስጠት ከግምት የሚልቅ በትንሹ አነስተኛ ጥናት ይጠይቃልና ተዓዝቦዬን በግርድፉ ላስቀምጥ፡፡ የመጀመሪያው መንስዔ [ግለሰባዊ ምልከታዬ መሆኑን ልብ ይሏል] ከታች የዳበረ የንባብ ባህል አለመኖር ይመስለኛል፡፡ (ያው በዘውግ ተከፍለው መታየት ቢችሉም ጥናት አልባ ተዓዝቦ ነውና ከምሁራዊ እይታ ዘወር ብለው ይረዱኝ፡፡) የመፃህፍት ዋጋ ውድነት፣ ያንባቢ ማህበረሰብ እንዳጠቃላይ አለመኖር፣ አሳሪ የሚባል ዓይነት የሐይማኖት አጥባቂነት (ይህች እንኳ ቅጥፈት ትመስለኛለች) ባህል፣ በተጨማሪም በግለሰብ ደረጃ ሊጠቀሱ የሚችሉ በርካታ ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡

ለምን እናነብባለን? ቀላሉ መልስ፣ ከላይ ለተጠቀሱትንም ሆነ ለሌሎች ችግሮቻችን (ይህ ዝብርቅርቅ ምናምን "ታሪካችን" ላይም) መፍትሔው የገዛ አስተሳሰባችን ለውጥ ነው፡፡ ይህ ለውጥ ከማንበብ የሚጀምር አይመስላችሁም? እጠይቃለሁ!

Urban legend (ያማርኛ ቃል አጣሁለት) ተብሎ የሚጠራው ራፕሩ ቱፓክ ሻኩር Changes በሚለው ዘፈኑ ላይ ይህንን ቃል ያወራል...

We gotta make changes... it's time for us as a people to start making some changes... let's change the way we eat, let's change the way we live, let's change the way we treat each other... you see the old way wasn't working... so it's on us to do... ...የለውጥን አስፈላጊነት ውበታዊ በሆነ መንገድ ለመረዳት ይህ ገለፃ በቂ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡


ብቻ ማንበብን በመታከክ የሚመጡ ጥያቄዎችን በ21ኛው ክፍለ ዘመን ጋር ተጣማጅ (Compatible) የሆነ ብቁ ሙተማመን በመሃላችን መኖሩን የሚያሳብቅ መልስ እንዳለን እጠራጠራለሁ፡፡ ቢያንስ በዚህ እርግጠኛ መሆን የሚያስችል ተመጋጋቢ ቁም ሓሳብ በጥቂቱ አንባቢያን ዘንድ ማዋቀር የተለመደ የዕለት ተዕለት ወሬ ሆኗል፡፡ አንድም ቀን አድርገን ስለማናውቀው "ነገር" መናገር ከጣቶቻችን ቁጥር ጋር የሚስተካከሉ ወዳጆቻችን ተፈጥሯዊ ባህሪ ሆኗል፡፡ ስቀን ሙተላለፉ ካንደበታችን በላይ የሚናገር አይመስላችሁም?


ትዝ ይለኛል! ትንሽ እያለሁ... መምህሩ "X (ኤክስ) በX ከጠፉ Y(ዋይ) በምን ይጠፋል?" ብሎ ቢጠይቅ አደባባይ ጥግ ብስክሌት እየጠገነ ሁሌ የጀላቲና የሸንኮራ አንዳንዴም የጫት ወጭውን መሸፈን የሚችለው (ከሁላችንም ጠንካራ ኢኮኖሚ ያለው) "ቶኒ" ነበር "በዳስተር ነዋ ቲቸር" ብሎ የመለሰው፡፡ ትውስታው ታትሟል!

ዛሬ ላይ ደግሞ እታዘባለሁ! Justify ማድረጋችን ጨኸታችን ውስጥ ገንኗል፡፡ አርአያ እንደማያስፈልገን "የሚያውቁ" ጥቂት ታላላቆቻችን «ወይ ትልቅ አይደሉም ወይ እኛን አያውቁም» ብለን መወረፍ መቻል ኢ-ጤነኛ ማፈንገጥን ያመላክታል፡፡ በመሃላችን የሚገቡት ደግሞ ይህን ያውቃሉ፡፡ የንቀትስ ፅንስ ያኔ "የሚጠነሰስ" አይመስልም? እጠይቃለሁ!

የንባብን ያይን ከፋችነትን ሚና በሚስብ መንገድ አሰናስሎ መኖር የፊት ሰዎቻችን የህልውና ወንዝ እንደሆነ ማወቅ ተስኖን ግለሰባዊ የህሊና ፀቦቻችን የህብረታችን መሊያ እስኪመስሉ ዓለሙ እንዳይታዘበን ፈራሁ?

አብረንስ "ፍቅርን" ፊራን እንዴ? ይኼኔ ነው የቱፓክን Changes መስማት የምፈልገው፡፡ ጥዑም ንባብ!!





ንባባችን

©በአንተነህ ዘ
(contemporaryanteneh@gmail.com)

በሚያነቃ መደመም (አግራሞት) ውስጥ የምትዶለን "ነገር" ናት ይሏታል፡፡ - ጥበብን (ውበትን)፡፡ "የሕግ ድምፅ" በተባለ "ሕጋዊ" (ነ) መፅሔት [እንዳይደለ የሚከራከር አይጠፋምና የብያኔ ክፍተት ትተናል] ላይ ለጥበብ ቦታ አይታጣምና እንደጨዋታ አድርገን ለዚህ Universal የዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ የምናካፍለው አለ ብለናል፡፡ እነሆ የቃላችን አሃዱ ለናንተ ይለፍ! ስለአብሮ ኗሪዎቻችን፣ ተመጋቢዎቻችን፣ ተማሪዎቻችን፣ ደፈር ብለን ደግሞ ስላስተማሪዎቻችን ላቅልምና፣ ንባብ ሰንቁያለሁ ስለሚሉን ነገራ ነበዛዝቶቻችን (ተጓደኞቻችን) ግስቁል ሓሳቦች ግለሰባዊ ስላቁን አቀብላለሁ፡፡

ጥበብ፣ [ሳይኮፓዝ ይላሉ አንዳንዶች አንዳንዶችን] ዘመን ማጉን በተፈጥሮ ሕግ እየደወረ በመጣ ቁጥር ማዕቀፉ እየሰፋ ዛሬ የሚያጠቃልላቸው ዘውጎች በርክተው ነጠላ ክህነት (Single specialization) ግዴታ እየሆነ መጥቷል፡፡ ሳይንሳዊ መሰረት ያለው የሕይወት አተያይ በራሱ ጥበባዊ ቅኝት አያጣውምና ጨዋታችን በአዲ-ሓቂ ይገደብ ብንል የውበትን ቀለም ከማደብዘዝ የላቀ ሰንካላ ስኬት ውጭ መውደቂያ የለንም፡፡ (የዚህ ፅሁፍ አዘጋጅ የወዲህኛው ግለሰባዊነት ላይ "ይሞኛልና" ወፍራም ቅንነት ያለው ልቦና ቢያነበው ይሻል፡፡)

ዱሮ! ዱሮ! (ከልደቴ ቀደም ብሎ ያለውን ጊዜ ዱሮ እያልኩ ብጠራ ከሳሽ የለኝምና) እዚህች እኛ አገር ዩንቨርሲቲ የሚገቡ ድንጉጥና ደፋር፣ ቁንጠኛና መናኛ ወጣቶች ትንታግ አንባቢያን እንደነበሩ ሕላዌ ያዘለቃቸው ነጋሪዎች ማንበባችውን የተዉ እስኪመስል ይህንኑ ደጋግመው እያወሩ ሊያደነቁሩን ቃጥቷቸዋል፡፡ (ቁም ነገሩ ትናንት ሳይሆን "የዛሬ ባለቤትነታችንን" ላይ አፅንዖት ቢኖረው ነው እላለሁ፡፡) እና "ያኔ" የነበሩ የዛሬዎቹን እኛን የመሰሉ ተማሪዎች የሥነ-ልቡና መነሻቸው ላይ ዝም ብንልም የሀገራችን ታሪክ ቀያሪ መሆን የሚያስችል ንቃትን ማዳበራቸው ላይ መወሻሸትን የሚፈቅድ ከመሃላችን የለም ማለት ይቻላል፡፡ የሆነው ሆኖ ዛሬ ከመፅሃፍ ገፅ ይልቅ የሰውን ገፅ ማንበብ "የሚችሉ" በርካታ የጀበና ቡና መሸጫ ጠረጴዛ ላይ የሚቀመጡ ትንታግ "ፊት አድማጮች" ሞልተውናል፡፡ ዓይንን የሚማርኩ I`m dope! የሚል ካናቴራ የሚለብሱ "ወንዶች" ወይም I`m pregnant የሚል "እጅ አጋላጭ" ጨርቅ የለበሱ "ሴቶች"ም ጊቢያችን አፍርታለች፡፡ ደስ ይላል!! (×2)

"የነፍስ ጥሪ" የሚሏት የብዕር ጨባጮች ሕይወታዊ ገለባ አለች፡፡ ምንም እንኳ ፀሃፊ ጥበባዊ ምልከታው ግዝፈቱ ቢተልቅም ለተዓዝቦው አድማስ ክፈፍ የለውም፡፡ ሕግ ትምህርት ቤት ባንድ ክፍለ ጊዜ ይህ ሆነ፡፡ ያስተምሩን የነበሩት የህግ ፕሮፌሰር የሚያስተምሩንን "ነገር" ላፍታ ተወት አድርገው የሚከተለውን ጥያቄ ጠየቁን፡፡ "የኩላሊት ሥራ ምንድነው?" ይህ ለምን ሆነ ብዬ ዘግቼም ቢሆን በጉዳዩ ላይ "ባያሌው ቆዝሜበታለሁ"፡፡ መምህራችን ይህን ጥያቄ ከጠየቁበት ምንያቶች አንዱ እየተማርን የነበረውን ትምህርት ላይ ስለዕለቱ ትምህርት ያለን እውቀት ውስን ከሚባለው ደረጃም ዝቅ ማለቱ መሰለኝ፡፡ የበለጠ አስቂኙ ነገር፣ እፍረትን ለክተን የለበስነው እስኪመስል ድረስ የኩላሊትን ሥራ ምን እንደሆነ ለመናገር አለመድፈራችን ነው፡፡ (በራስ መተማመን ላይ "ጥቀሱልኝ")

...የመምረጥ ጉዳይ የኛ ስብዕና መፈተሻዎች ናቸው፡፡ ሙከራችን ማበረታቻ፣ ትጋታችንም ሽልማት፣ ፅናታችንም ስኬትን ይወልዳሉ፡፡ የሁለንተን ሕግም ከሰውነት ሽቅብ በማህበራዊ ትስስር ቀዳዳ አንጋጠን ስንመለከተው ምንም ያህል ቢገዘፈ እነዚህ "እውነቶች" ያካተተ ነው...

ዘመናችን ለሞሞክር ማበረታቻ፣ ለሚተጋም ሽልማት አይነፍግም፡፡ (ላፍታ ሁለንተናዊ ለመሆን ሞክሮ ማየት...) ፅላሎቶቻችንን አራግፈን ጥለን በእጅ ሓልሰጥም መርሕ መነሳት መሰረታዊ ግብዑቱ መሆኑ ማስተዋልና ራስን ለመለወጥ (ለመለዋወጥ አላልኩም) ዝግጁ እስክንሆን ድረስ ማበረታቻው አይቀርብንም፡፡ (አሁን ይህንን የተተረፈረፈ "ሚስጥሩ" የሚል መፅሀፍ ያነበበ መቼም አያጣውም) እነዚህ የሉላዊነት ዘመን ላይ በርክተው የምናያቸው የመረጃ አውታሮቻችን ተቀዳሚ ልህቀት እውቀትና ቢዝነስ የሚያስገኙልንም መሆኑ ነው፡፡ ይህ የዘመን አስደናቂ ለውጥም ተዳሳሽ ምጥቀቱ እኛንም ንፍቀ-ክበቡ ውስጥ ለመሰደር ብዙ አለመልፋቱም ይመስላል፡፡ እውቀት፣ ሥራን፣ ጥበብን፣ ጊዜ "መግደያንም" ጨምሮ በርካታ አዎንታዊም አሉታዊም የሆኑ ተምኔቶቻችንን መቆናጠጫ መሳለጫዎቻችን በዘርፈ ብዙ አማራጮች ቀርበውልናል፡፡ የመምረጥ ጉዳይ የኛ ስብዕና መፈተሻዎች ናቸው፡፡ ሙከራችን ማበረታቻ፣ ትጋታችንም ሽልማት፣ ፅናታችንም ስኬትን ይወልዳሉ፡፡ የሁለንተን ሕግም ከሰውነት ሽቅብ በማህበራዊ ትስስር ቀዳዳ አንጋጠን ስንመለከተው ምንም ያህል ቢገዘፈ እነዚህ "እውነቶች" ያካተተ ነው ፡፡

መፈለግ... የፍላጎት ሓሳብ... ሓቂቃዊ የመሻት እርሾ ውስጣችን አለ? ስለንባብ ነጠላ ክር መዝገፍ ጨዋታችንን ልቀጥል... ከዚያ በፊት መምህራኖቻችን "ትከሻ ላይ ትንሽ ብንቆም" (አብረን) ምን ይለናል?

አብዛኛው ለማለት የሚያበቃ ምልከታ ባይኖርም ጥቂት ግን የማይባሉ መምህራኖቻችን አርአያ የመሆን ፍላጎታቸው (ሞራላዊና ሙያዊ ግዴታቸው ይመስለኛል) በማይተመን ደረጃ ዝቅ ይላል፡፡ ዘመነኛውን የግለሰባዊነት ፍልስፍናን የመከላከያ አቋማቸው ለማድረግ ቢሞክሩም በጊዜ በቦታና በሁኔታ የማይወሰን ፍልስፍና የለምና ለጣቂ ክርክሮቻችን ከጉንጭ አልፋነት አይዘልሉም፡፡ [በሌላ እትም ስለ "ዘመነኛው የግለሰባዊነት መንገድ" ላይ ጨዋታ ይኖረናል፡፡] ወቀሳ ቢያስመስልብንም የታየን መናገራችን ግን ሽንቋጭ ከሆነ አንዳች እውነት ጋር ጥምረት ወድዷል ማለት ይመስላል፡፡ ለወቀሳ መትጋት ባልፈልግም [ከተወቃሾች አንዱ ነኝና??] ማንበብን ተከትሎ የሚነገር "ውበት" ግን አለን ማለትም የብዙን ድፍረት ይመስለኛል፡፡

(ወደ ገፅ 9 ዞሯል)

McCartism

©በማርቆስ ጌታቸው
(markosgetachew968@gmail.com)

ጊዜው እንደአውሮፓውያን የዘመን ቀመር መሰረት ይቆጠራል፣ 1954 ዓ.ል፡፡ በወቅቱ ምድራችን በወቅቱ የአለም ኃያላን መንግስታት ዩ.ኤስ. አሜሪካ እና ሶቪየት ሕብረት መሓል የቀዝቃዛው ጦርነት የተቀሰቀሰበት ወቅት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ በጊዜው የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለምን የምታራምደው ሶቪየት ሕብረት መሬት ኢምፔሪያሊዝም አማራጭ መንገድ ሳይሆን ወንጀል እንደሆነ ሁሉ በዩስ አሜሪካ ሶሻሊስት መሆን በወንጀል ያስከስሳል፡፡

በዚህ ወቅት ነበር ሴናተር ጆሴፍ ማካርቲ "ወዳጆቼ ሀገራችን አደጋ ላይ ናት፡፡ ፓርላማ ካለው ተወካይ አብዛኛው በሶሻሊዝም `የሚያምኑ` ናቸው፡፡ መንግስት ሰራተኞችም መሓል የሚበዙት ሶሻሊስቶች ናቸው፡፡" ብለው በመቶዎች የሚቆጠሩ የስም ዝርዝሮችን ለሚዲያ አቀረቡ፡፡ ሆኖም ይህ ንግግር ያለምክንያታዊ መነሻ እና መረጃ መሆኑ በመረጋገጡ ትዝብት ላይ ጣላቸው፡፡ ከጊዜ በኋላም ዋልቅ ግንዛቤ ሳይኖር የሚደረግ ፍረጃን ከሴናተሩ ስም ተወስዶ McCartism ብሎ መዋራት ፋሽን ሆነ፡፡

— — —

እነሆ እኛም በሀገራችን በፖለቲካ፣ ኃይማኖት እና ታሪክን መሰረት ባደረጉ ውይይት ብሎም ክርክሮች ላይ መፈራረጅ እጅግ ተለምዷዊ መሆኑን ታዝበን እንፅፋለን፡፡

ፖለቲካ፡- ለንጉስ አፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት የዘመናዊ የትምህርት ተቋም መስፋፋት በተለይም በአፄ ኃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ (የአሁኑ አ፡አ ዩኒቨርሲቲ) መቋቋምን ተከትሎ የተነሳው የተማሪዎች ንቅናቄ በለውጥ ፈላጊውና የንጉሱን ስርዓት ከሚደግፉ መሐከል ከፍተኛ የሃሳብ ልዩነት በኋላም መቃቃርን ፈጠረ፡፡ ይህም ሁኔታ እያደገ ሄዶ በርካታ የፖሊቲካ ፓርቲዎችን ለመመስረት ቻለ፡፡ በኋላም አብዮቱን ቀልብሶ ወደ ሥልጣን የመጣው ኮሚኒስቱ ደርግ ሥልጣን ያዘ፡፡ ሆኖም ሰፊ ያሳብ ልዩነት በነበራቸው አካላት መሐል የነበረው የፅንፍ ለፅንፍ አመለካከት ባህል ሆኖ የቀጠለ በሚመስል መልኩ ሶሻሊስቶቹ (ኢ.ህ.አ.ፓ፣ መኢሶን፣ ደርግ፣ ወዘተ...) በአንድ ርዕዮተ ዓለም ጥላ ስር ቢሆኑም ጎራ ለይተው ሙተላለቅ ያዙ፡፡ "የኛ ወገን ያልሆነ የነሱ ነው" የሚል ፈሊጥ ያለምንም መሰረታዊ መሰረታዊ ግምገማና አመክንዮ ቃላት አንኳ የግለሰብን ጎራ እስከመወሰን ደረሰ፡፡ እንደአሪስጣጢለስ (Aristotle) The Golden Mean የሚል ሰው ሁለት ጥይት ምሱ ሆነ፡፡ ሁሉም ግለሰብ ጎራ አለው ፍረጃም ባህል ሆነ፡፡ ጎራ አለኝ ብለህ ባታምንም አኳኋንህ ታይቶ (አለባበስህ፣ አነጋገርህ፣ አዋዋልህ) ያለ አመክንዮአዊ መነሾ ያንዱ ጎራ መለዮ ይጠቀልልሀል፡፡ ግለሰብ የሚባል ነገር ከልቦናችን ተፍቆ ቡድን መለያችን ሆነ፡፡ እኔነት ጠፍቶ እኛነት ነገሰ...

ከዘመናት በኋላም ወታደራዊው መንግስት ተወግዶ ኢህአዴግ ስልጣኑን ከጨበጠ በኋላ ገዢና እና ተቃዋሚ ፓርቲ ተሰኝተው ተቃዋሚ ፓርቲነት እንደስሙ መቃወም ብቻ ገዢውም መልካም ጎኑ ብቻ እንዲለፈፍ አስተዋልን፡፡ በሙሉ ቀን ተቃውሞ መሃል አንድ ድጋፍ እንኳ ከተስተዋለ ቅዋረኛ፣ ባንዳ፣ በሚል ማስፈረጅ ያንደበታችን ሀሌታ ነበር፡፡ "የገዥው ፓርቲ ቃላትን" መጠቀም፣ ተቃዋሚዎችን መቃወም ወዘተ... ያለ ምንም ተጨማሪ ማስረጃ የእገሌ አልያ የእገሊት ፓርቲ አባላነት/ደጋፊነት ማረጋጫ ነው፡፡ የገዥው ፓርቲ ደጋፊ እንኳ ቢሆኑ የድርጅቱን ድክመት መናገር የተቃዋሚ ፓርቲነትን መታወቂያ ያሸልማል፡፡

ይህ በመሆኑም በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ላለማጣት በሚመስል አኳኋን ፖለቲካኞችም ይህን ስህተት ሲያራግቡት፣ ሓቁን መጋፈጥንም እንደጦር ሲፈሩት ማስተዋላችን እሙን ነው፡፡ ነገሩ ሁሉ ፅንፍ ለፅንፍ ነውና፡፡

ኃይማኖት፡- የመንግስትና የኃይማኖት መነጣጠል (Secularism) እውን ከመሆኑ ቀድሞ በካቶሊክ እና ኦርቶዶክስ ክርስትና እንዲሁም ኦርቶዶክስ ለሁለት ተሰንጥቆ አፄ ዮሀንስ "የመጨረሻ ውሳኔ" እስኪሰጡበት ድረስ በካራዎችና ፀጋዎች መሃከል አልፎ አልፎ ይካሄዱ ከነበሩ ክርክሮች በቀር በኃይማኖት ጉዳይ መከራከር/መወያየት እንግዳ ነገር ነበር፡፡ ኋላ ላይ በተለይም ከፕሮቴስታንት ኃይማኖት መጠናከርና መስፋፋት እንዲሁም ያማኝ ቁጥር መበርከት ተከትሎ በርካታ አይነኬ (ታቡ) የነበሩ ጉዳዮች ኃይማኖታዊ ልዩነትን ተከትሎ ቢሆን በመጠኑም መፈተሽ ጀመሩ፡፡

በፖለቲካ ውይይቶች ላይ ለማንሳት እንደተሞከረው በተመሳሳይ መልኩ ውይይቶች ጎራን መሰረት ያደረጉ ነበሩ፡፡ ቀዳሚው ነጥብ ምን ተናገረ? ሓሳቡ ምንድር ነው? የሚል ሳይሆን ኃይማኖቱ ምንድነው? የሚል በመሆኑ ውይይቶች ሁሉ ጉንጭ አልፋ ሆነዋል፡፡ አንድን ሃሳብ አንስቶ መጠየቅ የአንድን ቡድን መለዮ የሚያስለብስ አልያ የሚያስወቅስ ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ይህም የአእምሮን የፈጠራን አቅም በጅጉ መጉዳቱ እሙን ነው፡፡ እርግጥ ካመክንዮ አንፃር መዳኘት ውጤቱ ለብዙዎች "ያቀፉትን መጣል የወደቀውን ማንሳት" ያስከትላልና ቢያስፈራ አይገርምም፡፡ ሆኖም ቢያንስ ከፍረጃ ነፃ ለሆነ ውይይት ክፍት መሆን ሰው የመሆኛ አንዱ መንገድ መሆኑን እናምናለን፡፡

ታሪክ፡- ከሊቃውንት እስከ ተራ ተርታው ሕዝብ መግባባት ላይ ያልተደረሰበት የኢትዮጲያ ታሪክ ከዘመን ርዝማኔው (5 ሺህ፣ 3ሺህ፣ አንድ መቶ...) ጀምሮ በርካታ አከራካሪ ነጥቦችና ያልተመለሱ ጥያቄዎች መኖራቸው እርግጥ ነው፡፡

በተለይ ከማርክሲስት ሌኒኒስት (ማሌ) በወቅታዊ ግዥዎችና ወጣቶች ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ጋር ተያይዞ የናሽናሊዝም ጥያቄ መነሳት ጀመረ፡፡ ከዚህ ወቅት ጀምሮ ስለታሪክ ያለህ አተያይ ሓሳብህን መጠየቅ ሳያስፈልግ የመጣህበትን ብሔር ብቻ በመመልከት መፈራረጅ ባህል ሆነ፡፡ የምትናገረው አስተሳሰብም የእገሌ ብሔር ስለመሆኑ ተወስኖ በመቀመጡ፣ ሌላ ኃይማኖት ሆነን፡፡ ውይይትን ንቀን ስንነጋገር "በከየት መጣህ" ጥያቄ ብቻ መፈራረጃችን የኋላ ኋላ ብዙ መዓት ሳያመጣ አይቀርም፡፡ ግን ግን ይህን ፅሁፍ ያነበብ ሰው ከሆነ ጎራ ፈርጆኝ ይሆን?

ሻሎም!!

የስፖንሰር ቦታ

09 20 66 65 95

ልዩነት ለምን?

በሚኪያስ መላክ
(mikiasmelak@gmail.com)

ሰው እንደ መልኩ እና ቁመናው፣ ባህሪው እና ፍላጎቱ ክዚያም አልፎ አመለካከቱ፣ አዲስ ነገር አቀባበሉ እና አረዳዱ፣ ምርጫው እና አካሄዱ ሁሉ ይለያያል። ምንም እንኳ ሁሉም ሰው የሚጋራቸው እና የሚመሳሰልባቸው ብዙ ነገሮች ቢኖሩም ከላይ የጠቀስኳቸው ልዩነቶች የማይካዱ ናቸው። ነገር ግን በተለይ በአሁኑ ስዓት ከሚያመሳስለን ይልቅ የሚያለያየን፣ ከሚያስማማን ይልቅ የሚያጣላን፣ ከሚያግባባን ይልቅ የሚያከራክረን እና የሚያጋጨን ልዩነታችን ጎልቶ ይታያል። ልዩነት አይኑር አይባልም ምክንያቱም ይሄ ተፈጥሮን መፃረር እና መጣረስ ይሆናል። ገና ከጅምሩ የሰው ልጅ ፈጣሪ ልዩነትን እንደ ገፀ-በረከት አድሎናል እና ይሁን እንጅ ያ ልዩነት በትልቅ የአንድነት ክብ ውስጥ የታጠረ እና የተከበበ ስለሆነ ልዩነት ጎልቶ ለመታየት ቦታ አልነበረውም። በተለይም ከታሪክ እንደምንረዳው እና እንደምሰማው በሰዎች መካከል ልዩነት መኖሩ እስከማይታወቅ ድረስ አንድነት መገለጫቸው እንደነበረ የማይካድ እውነታ ነው። ፊደል ይገላል እንደሚባለው ዛሬ እማ እኛ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለልዩነት ዝግጁ ከመሆን ባሻገር በልዩነት ነዳጅ ተሞልተን፣ በልዩነት ተጉዘን፣ በልዩነት ብዙ እርቀን፣ በልዩነት ተወንፍፈን፣ ከአንድ ብረድስት የሚጨለፍ ወጥ እንኳ ያንዱ እየጣፈጠ የሌላው አልጣፍጥ እያለ እየተለያየን ተቸግረናል።ልዩነት **ለምን? ከሌላው በተሻለ መመሳሰል እና አንድ መሆን የነበረብን እኛ አልነበርንምን? ልዩነት ለምን?** በሀገር ወገን እና ቤተሰቦቻችን እምነት እኛ ተማሪዎች የነገ ፍሬዎች እንቁ ስንባል ተናፋቂ

የችግር ጎል ግብ ጠባቂ

ሁነን እያለን እኛ ግን ለምን እንዲህ?

ከማስፈቀድ መስረቅ፣ ከማበርታት ማዳከም፣ ከማሞገስ ማንቋሸሽ፣ ከማመስገን መሳደብ፣ ከመግባባት አለመግባባት፣ ከእውነት ይልቅ ውሸት፣ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ ገኖብን በልዩነት ጡፈን በካምፓስ እና በዲፓርትመንት በጣም እየከፋ ሲሄድ በባች እና በሴክሽን ተከፋፍለን አንድ መሆን አይደለም ምንም መሆን አቃተን። **ለምን?** እንድ እንድ ተማሪ ባለመቻሉ ወይም ባለማግኘቱ ስለሌለው ነገር የራሱን ድክመት እና ገመና ለመሸፈን ሲል የሌላን ተማሪ ስም እና ክብር ሲያጠፋ እና ሲያጎድፍ እሱ ከፍ ያለ እና የተሻለና ያጣውን ነገር ያገኘው ስለሚመስለው በትንሹም ቢሆን ከእሱ ተሽለው እና የተሳካላቸው የመሰለውን ተማሪዎች ሲያራክስ እና ሲያጣጥል ይውላል። **ለምን?** ስለሌላው የበታችነት ሲያወራ በተግባር ያጣውን ከፍታ ቢያንስ በወሬ ያገኘዋል። ቲቸር ለሚኪ A ሰጠው ለእኔ ደግሞ C። እንዴ ለምን አንዲህ አመጣህ ስትሉት ባክህ ሚኪ እኮ በራሱ ሰርቶ አይደለም ኮርጆ ወይም ተሰቶት ነው እንጅ እንዲህ አያመጣም። ስለዚህ እሱ ነበዝ በእራሱ ሰርቶ C ያገኘ። ግን ያልተጠየቀውን መመለሱ እንዳለ ሁኖ ሌላው ያደነቀውን እና ያሞገሰውን የተመሰከረለትን ሰው አምኖ ከመቀበል ውጭ አንተ ግን በማጣጣል እና ዝቅ ዝቅ በማድረግ መቸም ቢሆን የዚያን ሰው ቦታ ልትይዝ አትችልም። ላለመመሳሰል የልዩነት አባዜ ሰለባ ከመሆን ውጭ ጥቁር አንተ ስላልክ ብቻ ነጭ ሊሆን አይችልም። ያንተ የሆነ ነገር ሁሉ አንደኛ፣ አንተ የገባህበት ሁሉ ተመራጭ ግሩም ድንቅ የሚሆነው ሁኖ ሲገኝ እና ሲገኝ ብቻ ነው እንጅ የሌላውን ስላጣጣልክ አይደለም። ልዩነትን አትውደድ አታስፋው ይልቅ አጥበው። አንዱ የወደደውን ስለጠላህ ወይም አንዱ ያወደሰውን ስላጥላህ አንተ ልዩ ልትሆን ከቶ አትችልም ምክንያቱም በመቃረን ልዩነት የለም። በመወቃቀስ ልዩነት የለም። ልላውን ዝቅ በማድረግም ከፍታ የለም። የሎው ተማሪ ክብር የሌላውን ዲፓርትመንት ተማሪ ዝቅ በማድርግ ወይም በማጥላላት አይደለም። ክብሩ ሙያውና ስራው ነው። ለሌላውም እንዲሁ። ግን እኛ ተማሪዎች እንኳን ዲፓርትመንት ተለያይተን አንድ ዲፓርትመንትት ወይም አንድ ባች ኧረ አንድ ክላስ ሁነን ልዩነት እንፈልጋል **ለምን?** መለየት ለምን? መልሱን ለራስህ ወይም ለራስሽ ትቸዋለሁ። እኔ ግን እላለሁ አንድነት ለምን? ብትሉኝ፣ አንድነት ለፍቅር፣ ለመረዳዳት፣ ለማሸነፍ፣ ለሀይል እና ጥንካሬ ዘርፈ ብዙ በረከቶች በአንድነት ውስጥ አለ። **ከፊት የራቀህን ድረስበት እንጅ አትጎትተው። ከጫላህ ያለውን አትርገጠው ይልቅ ወድቆ ከሆነ አንሳው እንተም ወድቀህ እዳትሆን መሳለቂያው።**

እንጠያየቅ፤ በግቢያችን ብሎም በዶርማችን ስሙ ሲብጠለጠል የሚውለው ሳክስ ትርጉሙ ምንድን ነው? ትክክለኛ አጠቃቀሙስ? ምንጩ ከየት ነው? ከትግሬኛ፤ ከአማረኛ፤ከእንግሊዘኛ፤ ከግዕዝ፤ ከግሪክ. የብዙዎችን ማንነት እና ሁለንተና የተቆጣጠረው ሳክስ ማነው? የሳክስ ባለቤቶች እንደሚሉት ውሸት ማለት ነው? ወይስ ሌላ ትርጉም ይኖረው ይሆን፤ይሄም አንዱ የልዩነት መፍጠሪያ የውሸትካባ ነውን ወይስ ሌላ? በቀጣይ እትም እንገናኝ። የዚያው ሰው ይበለን።



ተከታዮችም ቢሆኑ “የአመራር ችግር ገጠመን”፤ "የመሪ ያለህ" እያሉ ከማማረራቸው በፊት “እኛ እንዴት ያለን ተከታዮች ነን” ብለው ራሳቸውን ቢጠይቁ የተሻለ መፍትሔ ለማግኘት ይረዳል።